# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 035 ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡ ኢዮብ ተፈራ

# “የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ለሉዓላዊነት የተከፈለ የኅብረ ብሔራዊ አንድነት ምልክት ነው”

-ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ

ገጽ 4

## የንግድ ማጭበርበርን ለመከላከል በተሠሩ ሥራዎች ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ማዳን ተችሏል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የሕግ ተገዢነትን ለማረጋገጥና የንግድ ማጭበርበርን ለመከላከል በተሠሩ ሥራዎች 50 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር የሚገመት ሀብት ማዳን እንደተቻለ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ ኮሚሽኑ 88 ቢሊዮን 100 ሚሊዮን ብር ገቢ ሰብስቧል።

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ የተቋሙን የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈጻጸም አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ ባለፉት ሦስት ወራት በተከናወነ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ሀገር ልታጣ የነበረውን 50 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ማዳን እንደተቻለ ገልጸዋል፡፡ ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ78 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል ብለዋል፡፡

ተቋሙ የሕግ ተገዢነትን ለማረጋገጥና የንግድ ማጭበርበር የመከላከል ሥራዎችን

የንግድ ማጭበርበርን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ሐዲሽ አብርሃ

## “ማዕቀፉ ወደ ሕጋዊ ተፈጻሚነት መምጣቱ በእኩልና በፍትሐዊነት የመጠቀም መብትን የሚያረጋግጥ ነው”

ኢንጂነር ሐብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) -የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ወደ ሕጋዊ ተፈጻሚነት መምጣቱ ኢትዮጵያ ስታራምድ የነበረውን በእኩልና በፍትሐዊነት የመጠቀም መብትን የሚያረጋግጥ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ገለጹ።

“ማዕቀፉ ወደ ሕጋዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “የሀገርን ክብር ከፍ ለማድረግ ቀን ሳይወስኑ ሁሌም መትጋት ይገባል”

-አቶ አደም ፋራህ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የሀገርን ክብር ከፍ ለማድረግ ቀን ሳይወስኑ ሁሌም መትጋት ይገባል ሲሉ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊና የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ገለጹ።

17ኛው ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን “ሰንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ከፍታ!” በሚል መሪ ሃሳብ በብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽሕፈት ቤት ትናንትና ተከብሯል።

በወቅቱ አቶ አደም ፋራህ እንደተናገሩት፤ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችንን ከማክበር ባለፈ እያንዳንዱ ዜጋ በተሰማራበት ሙያ በየዕለቱ የሀገሩን ክብር ከፍ ለማድረግ መጣር ይኖርበታል። በተገቢው ቦታና ጊዜ ሁሉ የሀገርን ሰንደቅ ከፍ ለማድረግ ጠንክሮ መሥራት ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ብሔራዊ ሰንደቃችንን ማክበር ማለት ለሀገር ሲሉ ለተዋደቁት ክብር መስጠት ነው ያሉት አቶ አደም፤

“የሀገርን ክብር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ፎቶ፡ በሪሁን ታደሰ

ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ ፊታሞ

# በማሠልጠኛው የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ሠራዊቱ ከመንግሥት በጀት ጥገኝነት እንዲላቀቅ የሚያደርጉ ናቸው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡-የጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግተኛ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት በግቢው የተጀመሩ የግብርና ልማትና የፈርኒቸር ሥራዎች ሠራዊቱ ከመንግሥት በጀት ጥገኝነት እንዲላቀቅና በምግብ እራሱን እንዲደግፍ ማስቻሉን አስታወቀ።

የጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግተኛ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ዋና አዛዥ ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ ፊታሞ እንደገለጹት፤ በማሠልጠኛው የተጀመሩ የግብርና ልማትና የፈርኒቸር ሥራዎች ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል።

ትምህርት ቤቱ ዳር ድንበር ለመጠበቅ ደምና ላባቸውን ገብረው የሀገርን ሉዓላዊነትን የሚያስከብሩ ወታደሮች ከማሠልጠን ጎን ለጎን ከ87 ሄክታር በላይ የተለያዩ እርሻ ሥራዎች፣ የከብት እርባታ፣ የንብ ማነብ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የተለያዩ ቋሚ ተክሎችና የፈርኒቸር ውጤቶች እየለሙ ይገኛሉም ነው ያሉት።

እንደ ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ ገለጻ፤ በ2016/17 በመኸር እርሻ በግቢው ከ85 ሄክታር በላይ በቆሎ ተዘርቶ ከ4 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል። በቦረና ድርቅ ጊዜ ዘር ለማቆየት ተብሎ የመጡ የቦረና ከብቶች በከፍተኛ እንክብካቤና ትጋት በተሠራው ሥራ ዘር ከማቆየት በተጨማሪ ሠልጣኙ የወተት ተዋፅዖ እንዲያገኝ አስችሏል።

በተጨማሪም የበቆሎ ምርቱ ወታደሩ ይበላው የነበረውን የሩዝ ምርት በበቆሎ ቅንጬ ለመተካት አስችሏል።

ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ አክለውም፤ በመኸር እርሻ ከተመረተው በተጨማሪ በበጋ መስኖ የሽምብራ እርሻ ዝግጅት እየተደረገ ነው ያሉ ሲሆን በግቢው በፈርኒቸር ውጤት በተሠራ ሥራ ከአንድ ሚሊዮን 500 ሺህ ብር በላይ ወጪ ማዳን መቻሉን ጠቁመዋል።

ወታደር አምራች ሳይሆን የተመረተውን በመጠቀም ሀገርን የሚጠብቅ ብቻ እንደሆነ የሚታሰብ ቢሆንም ማሠልጠኛው ሀገራዊና ወገናዊ አስተሳሰብን መርሕ በማድረግ በተሠሩ የተለያዩ የልማት ሥራዎች ከሠራዊቱ ተጠቃሚነት አልፎ ለአካባቢው ማኅበረሰብ እየጠቀመ መሆኑን ተናግረዋል።

ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ፤ በግቢው ከሚሠሩ የልማት ሥራዎች በተጨማሪ የአካባቢውን ሥነ-ምሕዳር ከመጠበቅና በማሠልጠኛው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የዱር አራዊት እንዲጠበቁ መደረጉንም ጠቅሰዋል።

ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ የማረሻ ትራክተር እንዲሁም በአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን አምስት የውሃ ፓምፖች በባለፈው ዓመት ከተመረተው ምርት መገዛቱን አስረድተዋል።

ማሠልጠኛው ከተጣለበት ሀገራዊ ኃላፊነት በተጨማሪ ያከናወናቸው በርካታ የልማት ሥራዎች ለሌላው ማሳያ የሚሆን ነው ያሉት ብርጋዴል ጄኔራል ጡምሲዶ፤ በዚህም በተለይ ለሠራዊቱ ተኪ ምግቦች ማቅረብ መቻሉን አብራርተዋል።

# ትምህርት ቤቶች ደም ልገሳን በባለቤትነት መንፈስ እንዲያስተባብሩ ጥሪ ቀረበ

**ሶሎሞን በየነ**

አዳማ፡- እንደሀገር ያለውን የደም ፍላጎትና አቅርቦት ክፍተት ለማጣጣም ትምህርት ቤቶች ደም ልገሳን በባለቤትነት መንፈስ በማስተባበር የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የኢትዮጵያ ደምና ኅብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ጥሪ አቀረበ።

የኢትዮጵያ ደምና ኅብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት "ደም በመለገስና ሌሎችም እንዲለግሱ በማሳሰብ ሕይወትን እናስቀጥል" በሚል መሪ ሀሳብ የበጋ ወቅት የደም አሰባሰብ ሁኔታ ላይ ከትምህርት ተቋማት ፎረም ጋር በአዳማ ከተማ ከትናንት በስቲያ የምክክር መድረክ አካሂዷል።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ደምና ኅብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር በ2016 ዓ.ም 349 ሺህ ዩኒት ደም የተሰበሰበ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 51 በመቶ የሚሆነው ደም የተሰበሰበው ትምህርት ቤቶች ላይ ነው።

ስለዚህ እንደሀገር ያለውን የደም ፍላጎትና አቅርቦት ክፍተት ለማጣጣም የትምህርት ቤቶች ሚና አይተኬ መሆኑን በመረዳት፤ ትምህርት ቤቶች ደም ልገሳን በባለቤትነት መንፈስ እንዲያስተባብሩ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አቅርበዋል።

ሆኖም ክረምት ላይ ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ ከፍተኛ የደም እጥረት እንደሚገጥም የሚናገሩት አቶ ሀብታሙ፤ ትምህርት ቤቶች በቀጣይ የክረምት ልገሳ መርሐ ግብር በቋሚነት በማዘጋጀት በክረምት ወራት የደም እጥረት እንዳይከሰት እና ዜጎች በደም እጦት ሕይወታቸውን እንዳያጡ ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

የደም ልገሳ ባሕሉ እያደገ ቢመጣም የዓለም ጤና ድርጅት ካስቀመጠው መስፈርት አኳያ ገና ብዙ የቤት ሥራ ይቀራል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤



አቶ ሀብታሙ ታዬ

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት መስፈርት ከአንድ ሀገር ሕዝብ ውስጥ አንድ በመቶው ቋሚ ደም ለጋሽ መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ።

ነገር ግን ለአብነት በ2016 ዓ.ም እንደሀገር ከተሰበሰበው 349 ሺህ ዩኒት ደም አኳያ በቋሚነት እየለገሰ ያለው ማኅበረሰብ 0.3 በመቶ እንደሆነ ይናገራሉ።

ትምህርት ቤቶች የተቋቋሙበት ዋና ዓላማ በማኅበረሰቡ ዘንድ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ማስተማርና ማኅበረሰቡን መጥቀም ነው የሚሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከዓለም ጤና ድርጅት መስፈርት አኳያ ያለውን የደም ፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን ለማቀራረብ ደም በመለገስና ሌሎችም እንዲለግሱ በማስተማር ሕይወትን በማስቀጠል የበጎ ፍቃድ ሥራ ላይ ትምህርት ቤቶችና መምህራን ሙያዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል።

በዓመታዊው የትምህርት ተቋማት ፎረም የበጋ ወቅት የደም ማሰባሰብ የምክክር መድረኩ ላይ የአገልግሎቱ፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ መምህራን ተሳትፈዋል።

በመድረኩም ስለ ደምና አይን ብሌን ልገሳ የመድረኩ ተሳታፊዎችን ግንዛቤ ከፍ የሚያደርጉ ጽሑፎችን ባለሙያዎች አቅርበዋል።

# ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎችን የጤና መድን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ ዓመት ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ የመዲናዋ ነዋሪዎች አቀፍ ጤና መድን ተጠቃሚ ለማድረግ ዕቅድ መያዙን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አስታወቀ። የ2017 ዓ.ም የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድን የአባልነት ምዝገባ እየተካሄደ መሆኑንም ገልጿል።

የ2017 ዓ.ም የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድን የአባልነት የምዝገባ ጊዜ ከጥቅምት 1 እስከ ኅዳር 30 ቀን ድረስ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ጤና ጣቢያዎች የነባር እና አዲስ አባላት ምዝገባ መካሄድ መጀመሩን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተናገሩት፤ የ2017 ዓ.ም የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድን ነባር አባላቶች ሙሉ ለሙሉ እድሳታቸውን እንዲያከናውኑ እና በዘንድሮው ዓመት አዲስ አባላቶችን ጨምሮ በአጠቃላይ ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ የከተማዋን ነዋሪዎች ተጠቃሚ ለማድረግ እቅድ መያዙን ገልፀዋል።

በከተማ አስተዳደሩ በፀደቀው መዋጮ መጠን መሠረት መደበኛ መዋጮ መጠን አንድ ሺህ 500 ብር ሲሆን የድሀድሃ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ በከተማ አስተዳደሩ እንደሚሸፈን ተናግረዋል።

ይህ ማለት ነባር አባል መዋጮ አንድ ሺህ 500 ብር፣ አዲስ አባል መዋጮ አንድ ሺህ 500 ብር እና የመመዝገቢያ 200 ብር በላይ አንድ ሺህ 700 ብር ዓመታዊ መዋጮ ይከፍላል ነው ያሉት።

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ ልጆች እና በአባሉ ጥላ ስር ለሚኖሩ ተጨማሪ ቤተሰብ 750 ብር እንደሚከፍል አመልክተው፤ በኢ-መደበኛ ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች



ዶክተር ዮሐንስ ጫላ

የተቀመጠውን መዋጮ በመክፈል ዓመቱን ሙሉ በሁሉም ውል በተገባባቸው የጤና ተቋማቶች አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ተናግረዋል።

ዋናው ነገር ጤና ነውና ኅብረተሰቡ ዛሬ ነገ ሳይል የምዝገባ ጊዜው አጭር መሆኑን ተረድቶ በሚኖርበት ወረዳ ጤና ጣቢያ በመሄድ ምዝገባ ማድረግ እንደሚገባም አሳስበዋል።

ኅብረተሰቡ ራሱንና ቤተሰቡን ካልታሰበ የድንገተኛ ወጪ ለመጠበቅ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድን አባል መሆን እንዳለበት እና አባላት ወደ ምዝገባ ሲሄዱ መሟላት የሚገባውን በሙሉ በሟሟላት ሥራው የተቀላጠፈ እንዲሆን ማገዝ እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል።

የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድን መርሕ መደጋገፍ ስለሆነ አባላት ቢታመሙም ባይታመሙም ሕመም ወይም በሽታው መቼ እንደሚገጥም ስለማይታወቅ አባልነታቸውን በወቅቱ ማደስ ይኖርባቸዋል ብለዋል። ያልተመዘገበ ወይም አባልነቱን ያላደሰ አገልግሎቱን ማግኘት እንደማይችልም ተናግረዋል።

በ2016 ዓ.ም ከሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዜጎች በላይ በማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድን አባል የሆኑ ሲሆን ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ አባላትና ቤተሰቦቻቸው በተመላላሽ እና በተኝቶ ሕክምና ከጤና ጣቢያ ጀምሮ እስከ ፌደራል ሆስፒታሎች ባሉት የጤና ተቋሞች የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በ2016 ዓ.ም ከተማ አስተዳደሩ ለማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አንድ ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ድጎማ ማድረጉንም አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት
Ethiopian Meteorology Institute

## በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ተገለጸ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመካከለኛው፣ በምሥራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ከአማራ ክልል በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግኸምራ፣ ሰሜን ሸዋ እና የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ አዲስ አበባ፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢፕድ በላከው የትንበያ መረጃ አመላክቷል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙም ኢንስቲትዩቱ አስታውቋል። ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ምሥራቅ ፣ደቡብ ምዕራብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውም ተገልጿል።

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምሥራቅ ባሌ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምሥራቅ ቦረና ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዴኦ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ፣ አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከሶማሌ ክልል ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን፣ ቆራሂ ዶሎ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር እና ሸበል ዞኖች፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ቀላልና መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ተጠቁሟል።

የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ በነበሩት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረው ተመላክቷል። እንዲሁም በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ጋር ተያይዞ በምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ከፋ፣ ሸካና ማጂ አካባቢዎች ላይ በጥቂት ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።

ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምሥራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፣ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኙዋ እና ማጃንግ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይም ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ተጠቅሷል።

ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ጎጃም፣ የሰሜን፣ የደቡብ እና የማዕከላዊ ጎንደር፣ አዊ ዞኖች እና ባሕርዳር ዙሪያ፣ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያው ጠቁሟል።

# ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ለመቻል ግብርናው ላይ ትኩረት አድርጋ እየሠራች ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ለመቻል ግብርናው ላይ ትኩረት አድርጋ እየሠራች ነው ሲሉ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋው (ዶ/ር) ገለጹ።

በምግብ ሥርዓትና በአግሮኢኮሎጂ ላይ ያተኮረው የመጀመሪያው የአፍሪካ ወጣቶች ጉባዔ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋው (ዶ/ር) በጉባዔው መክፈቻ ላይ እንዳሉት፤ አፍሪካ በምግብ እራሷን አለመቻሏ ለበርካታ ችግር አጋልጧታል።ከእነዚህም መካከል ተደራራቢ ግጭቶችና ሠላም ማጣት ዋነኞቹ ናቸው።እነዚህንና ሌሎች ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታትም በምግብ እራስን መቻል የቅድሚያ ተሰጥቶት መሥራት ያለበት ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡



በኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ለግብርናው የሚገባውን ያህል ትኩረት ሳይሰጥ ቆይቷል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ሀገሪቱ በምግብ እራሷን ለመቻል በግብርናው ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በግብርናው ዘርፍ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት፣ ሜካናይዜሽንን በማበራከት፣ ኩታ ገጠም እርሻን በማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ የግብዓት አቅርቦትን የማሳደግና በወቅቱ ተደራሽ የማድረግ ተግባር መከናወኑን ጠቅሰዋል።ለአብነትም የማዳበሪያ አጠቃቀም ከነበረበት 13 ሚሊዮን ኩንታል በ2016 የምርት ዘመን ወደ 20 ሚሊዮን ኩንታል ከፍ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ዘንድሮ 24 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመግዛት መታቀዱን ገልጸው፤ በኢትዮጵያ ያለው የማዳበሪያ አጠቃቀም በአምስት ዓመት ውስጥ በእጥፍ አድጓል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የሜካናይዜሽን ሥራውን አጠናክሮ በመቀጠል ከትራክተር ጀምሮ እስከ ወተት ማለቢያ ያሉ ማሽነሪዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በማድረግ ሀገሪቱ በምግብ እራሷን ለማስቻል ቅድሚያ ተሰጥቶት የሚሠራ መሆኑ ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ጉባኤው በዋናነት የምግብ ሥርዓቱን ለማስተካከል ግብርና ላይ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ላይ መሥራት አለበት በሚሉ ጉዳዮች ላይ ለመምከር የተዘጋጀ መሆኑን ያነሱት ፍጹም (ዶ/ር)፤ የአፍሪካ የምግብ ሥርዓትና ሉዓላዊነት በአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ እየደረሰበት በመሆኑ የአሕጉሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ግብርናው ላይ እንዴት መሥራት ይቻላል? የሚለው ላይ መፍትሔ ለማምጣት የሚመክር መሆኑን ገልጸዋል።

ጉባኤው በመዲናዋ አዲስ አበባ መካሄዱ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናዋን ለማረጋገጥ የስንዴ እና የሌማት ትሩፋት ንቅናቄዎችን እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ እየተሠራ ያለው አረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ እንዲሁም በቱሪዝም ዘርፉ ያላትን ልምድ ለማካፈል ይረዳል ብለዋል፡፡

ጉባኤውን ያዘጋጀው አላይንስ ፎር ሶቨርኒቲ ኢን አፍሪካ (AFSA) ዋና አስተባባሪ ሚሊዮን በላይ (ዶ/ር)፤ ጉባዔው ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ከ45 የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ ከ250 በላይ ወጣቶች በአካል እንዲሁም ከሁለት ሺህ በላይ ወጣቶች በኦንላይን እየተሳተፉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ጉባዔው የአፍሪካን ግብርና ሥነ ምሕዳርና ብዝኃ ሕይወት የመጠበቅን እንደ ዋና ጉዳይ አድርጎ የሚካሄድ መሆኑን ተናግረው፤ አፍሪካ የምግብ ሉዓላዊነቷን ለማረጋጥ ሁሉም የእሴት ሰንሰለት በራስ አቅም ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል ብለዋል ፡፡

ጉባዔው በቀጣይ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በየሁለት ዓመቱ እንደሚካሄድ ታውቋል፡፡

# የጤና አገልግሎት ተደራሽነትንና ፍትሐዊነትን ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶችን መጠቀም ያስፈልጋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የጤና አገልግሎት ተደራሽነትንና ፍትሐዊነትን ለማሳደግ የሀገር ውስጥ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ተገለጸ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር፣ ቬክናነሰ ኦርቢት ሄልዝ በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ትላንት ተፈራርመዋል።



የጤና ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ በስምምነቱ ላይ እንደገለጹት፤ ለጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ለማሳደግ በቴክኖሎጂ የታገዘ የሀገር ውስጥ የፈጠራ ውጤቶች ያስፈልጋሉ።

ስምምነቱ የጤና መረጃዎችን ከማዘመን በተጨማሪ የመረጃዎችን ደህንነት መጠበቅ፣ ተደራሽነት መጨመርና ማዘመን ያስችላል ያሉት ዶክተር መቅደስ፣ ቴክኖሎጂን ከጤናው ዘርፍ ጋር በማስተሳሰር ለኅብረተሰቡ ፈጣንና ተደራሽ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ነው ብለዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር (ዶ/ር) በለጠ ሞላ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያን በዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ወደ ፊት ለማራመድ ተቋማት ያላቸውን አቅም በማስተባበር ሊሠሩ ይገባል።

ስምምነቱ በጤና ጥበቃው ዘርፍ የማኅበረሰቡን ችግር በብዙ መልኩ ሊያቃልል፣ ልማትንና የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታን ሊያፋጥን እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ በዘርፉ ወጣቶች ክህሎቱን ታጥቀው ቴክኖሎጂውን ማምረት፣ ወደ ውጪ መላክ የሚቻልበትን አቅም ለመገንባት እንደሚረዳም ገልጸዋል።

ከውጪ እያስመጣን የምንጠቀማቸው ቴክኖሎጂዎች ፋይዳ ቢኖራቸውም ተጋላጭነት አላቸው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ቴክኖሎጂን በሀገር ውስጥ መፍጠር የሚያስችል አቅምን ለማሳካት የተደረገ ጅማሮ ነው ብለዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል እንደተናገሩት፣ ሁለንተናዊ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ለወጣቶች አዳዲስ እውቀትና ክህሎቶችን ማስታጠቅ ያስፈልጋል።

በአምስት ተቋማት መካከል የተደረገው ስምምነት በተቋማት መካከል የትብብር ባሕልን ለመፍጠር ያስችላል ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፣ የመንግሥትና የግሉን ዘርፍ መካከል ያለውን አቅም አስተሳስሮ በመሄድ በፍጥነት ለመልማት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ስምምነቱ ኢትዮጵያን ከቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ወደ አምራችነት በሂደት የሚያሸጋግር ሥራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተለይም ቴክኖሎጂን መጠቀም ብቻ ሳይሆን በማምረት ለሌላውም መትረፍ እንደሚያስችልም ገልጸዋል።

የሀገር ውስጥ ምርትን ለመጠቀም፣ ጥራት ያለው የሥራ ዕድል ከመፍጠር ረገድ የራሱ የሆነ አበርክቶ እንደሚኖረውም በመግለጽ፣ ኢትዮጵያ የጀመረችውን ራስን የመቻል ጉዞንና በሁሉም መስክ ሁለንተናዊ ሉዓላዊነትን የማረጋገጥ ትልም እውን ሊያደርግ እንደሚችል ተናግረዋል።

የኦርቢት ሄልዝ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ፓዚዮን ቸርነት በበኩላቸው፣ ሀገር በቀል ኢኮኖሚንና እውቀትን እውን ለማድረግ ትብብር አስፈላጊ ነው።

እንደሀገር ዘመኑ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ መድረስ ካልተቻለ ወደኋላ መቅረት እንደሚመጣ ጠቅሰው፣ የካምፓኒውም ዓላማ ትርፍ ሳይሆን ቴክኖሎጂውን ማሳደግ መሆኑን ገልጸዋል።

# “የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ለሉዓላዊነት የተከፈለ የኅብረ ብሔራዊ አንድነት ምልክት ነው”

**-ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ**

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ለሉዓላዊነት የተከፈለ፣ የኅብረ ብሔራዊ አንድነት ማሳያ፣ የነፃነት፣ የእኩልነት ምልክት እና ኢትዮጵያውያን በከፈሉት መስዋዕትነት በትውልድ ቅብብሎሽ ጸንቶ የቆየ ዓርማ ነው ሲሉ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ገለጹ።

በሃገር አቀፍ ደረጃ ለ17ኛ ጊዜ «ሰንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ከፍታ» በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት በተከበረው የብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ፕሬዚዳንት ታዬ፤ ኢትዮጵያውያን ለሰንደቅ ዓላማ የሚገባውን ክብር ሊሠጡና እንደብሔራዊ በዓል ሊያከብሩት እንደሚገባም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በኢትዮጵያውያን ብቻ ታትሞ የቆየ ብሔራዊ መለያ ብቻ አይደለም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በአፍሪካውያንና በመላው ጥቁር ሕዝቦችም ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው የነፃነትና የእኩልነት ንቅናቄ ዓርማ ምልክት መሆኑንም ተናግረዋል።

የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማን ትርጉም ባለው መልኩ ማክበር ለብሔራዊ መግባባት፣ ለአብሮነት ለኢትዮጵያ አንድነት እና ሉዓላዊነት መጽናት እጅግ አስፈላጊና መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በዓሉ ሲከበር ኅብረብሔራዊ አንድነትና ሉዓላዊነትን ለሕልውና ዋስትና መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው። ኢትዮጵያ የመልከ ብዙ ባሕሎች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ፍላጎቶች፣ አስተሳሰቦች፣ በርካታ ሀብቶችና ልዩ ልዩ መልክዓ ምድር ያላት ሃገር መሆኗን በውል በመገንዘብ በብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ስር በጋራ መሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን በውል በማመላከት ሊሆን እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ብዙ ሆና አንድ፤ አንድ ሆና ደግሞ ብዙ ነች ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የዚህ መገለጫው ደግሞ ሰንደቅ ዓላማ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር ጠንካራ ሃገረ መንግሥት ለመገንባት እና የኢትዮጵያን ከፍታ አስተማማኝ መሠረት ላይ ለማኖር የሚቻለው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማን ከፍ በማድረግ፣ በተሠማራንበት ጠንክረን በመሥራት ነው ብለዋል።

ከትናንት እስከዛሬ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በደማቸው ሉዓላዊነቷንና ነፃነቷን አስጠብቀው ያኖሯትን ሀገር ዛሬ በእውቀታችን፣ በጉልበታችንና በላባችን ማልማት አለብን ብለዋል።

ያሉብንን የዘመናት ዕዳዎች ወደሀብት በመቀየር በታላቅ ተስፋና ነገን በማለም በአብሮነት ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ በማድረግ ለኢትዮጵያ ከፍታ ለመሥራት ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ቆርጦ መነሳት ይገባልም ሲሉ ተናግረዋል።

ሉዓላዊነቷን በዘላቂነት ማስከበር የሚቻለው ከልመና ነፃ ማውጣት ሲቻል በመሆኑም ትውልዱ በተሰማራበት ዘርፍ በእውቀትና በላቡ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ መረባረብ እንደሚኖርበትም አሳስበዋል።

ትውልዱ የራሱ ሀገራዊ ዐሻራ የሆነውን የህዳሴ ግድብን በአንድ ልብ፣ በአንድ ሃሳብ በራሱ እውቀት፣ ጥረትና ላብ ገንብቶ በማጠናቀቅ ኃላፊነቱን እንደተወጣ ሁሉ የሀገርን ሁለንተናዊ ብልፅግና ማረጋገጥ የትውልዱ ከፍተኛ ኃላፊነት ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያን ሠላም፣ ልማትና ሕልውና ለማስከበር መስዋዕት የሚከፍሉትን የመከላከያ፣ የፀጥታ አካላት፣ የእድገትና የልማት ኃይሎች በሙሉ ክብር ይገባቸዋል ብለዋል።

የሃገርን ሠላም የሚያውኩ ከኋላቀር አስተሳሰባቸው በማምከን ለሰንደቅ ዓላማ ክብር በመቆም ታሪካዊ ኃላፊነትን መወጣት ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።

ትውልዱ የተጀመሩ ሃገራዊ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሪፎርሞችን በተሟላ መልክ በመፈጸም ከአባቶች የወረሰውን የሃገርና የነፃነት ሰንደቅ ዓላማን ጠብቆ በማቆየት ታሪካዊ ኃላፊነትን መወጣት ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የብሔራዊ ኅብረታችንና አንድነታችን ማሳያ፣ የዜጎች ሃገራዊ ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት መገለጫ፣ ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ ትስስር እና የሥነልቦናዊ አንድነት የሚንፀባረቅበት ምልክት መሆኑንም ነው አምባሳደር ታዬ የተናገሩት።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ሰንደቅ ዓላማ የመስዋዕትነት፣ የነፃነት፣ የሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት ዓርማ ነው። የነፃነት፣ የሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት መገለጫ እሴት የአብሮነት ዓርማ ምልክት ነው።

ሰንደቅ ዓላማ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ውድ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለው በክብር አስጠብቀው በክብር ያስረከቡን በልባችን ታትሞ የቆየ የአሸናፊነት እና የነፃነት ዓርማችን ነው።

ኢትዮጵያ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ ታፍራና ተከብራ የቆየች ታላቅ አፍሪካዊ ሀገር ናት ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በመንግሥታዊ አስተዳደር ሥርዓትም ረጅም ዓመታት ካስቆጠሩ ሀገራት ተርታ የምትጠቀስ መሆኗንና የሰንደቅ ዓላማ ታሪኳም ከሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ጋር የተቆራኘና የተሳሰረ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ሀገራዊ ነፃነታችንና ሉዓላዊነታችንን ለመንጠቅ በየዘመናቱ በተደጋጋሚ የውጭ ወራሪ ኃይሎችን እናት አባቶች በተባበረ ክንድ ባንድነት ቆመው መክተውና አሳፍረው የመለሱት ለሃገራቸውና የነፃነታቸው መገለጫ ለሆነው ሰንደቅ ዓላማ ከሚሰጡት ክብር፣ ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት በመነሳት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን የሀገር ሉዓላዊነት እንዲከበር የሕዝቦች ነፃነትና ክብር ለማጽናት ለሰንደቅ ዓላማቸውና ለሀገራቸው ፍቅርና ክብር ሲሉ በአንድነት መስዋዕትነትን መክፈላቸውንም አስታውሰዋል።

በእለቱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምሕረት የቃለመሐላ ሥነሥርዓት ያስፈጸሙ ሲሆን፤ እለቱ በየዓመቱ እየተከበረ የሚገኘውም የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001 በደነገገው መሠረት መሆኑ ይታወቃል።

## “ማዕቀፉ ወደ ሕጋዊ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሐብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ተፈጻሚነትን አስመልክተው ትላንት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፣ የናይል ወንዝ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት በአፍሪካ ኅብረት በኩል ሕጋዊ ወደ ሆነ የጋራ ማዕቀፍ ተፈጻሚነት መግባቱን አስታውቀዋል። ኢትዮጵያ ስታራምድ የነበረውን በእኩልና በፍትሐዊነት የመጠቀም መብትን የሚያረጋግጥ መሆኑንም ገልጸዋል።

ማዕቀፉ፤ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ልማት ማከናወን እያሰበች በተለያዩ ምክንያቶች ስሟን በማጠልሸት ከወንዙ እንዳትጠቀም በማድረግ አሳሪ ሕጎች ነበሩበት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህን ሕግ በመሻር ለኢትዮጵያና ሌሎችም ሀገራት ጭምር ሊጠቅም ወደሚችል ሕጋዊ ተፈጻሚነት መሸጋገሩን አንስተዋል። ይህም ዓባይን የታችኛው ተፋሰሰ ሀገራት በበላይነት እንዲጠቀሙ ያደረገውን ሁኔታ የቀየረና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

ስምምነቱ ላይ 15 ዋና ዋና መርሆዎች ያሉት ሲሆን፤ እነዚህም ከመጠቀም፤ የውሃ ሀብቱን ከመጠበቅና መንከባከብ ጋር የተገናኙና ተፋሰሱ ላይ ልማት በማከናወን ዘላቂ አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተገናኙ ጉዳዮች የተካተቱበት ነው ብለዋል።

የናይል ወንዝ ትብብር ስምምነት ማዕቀፍ በታችኛው የዓባይ ወንዝ ተፋሰስ ያሉ ግብፅና ሱዳን በነባር ሕጎች እነርሱን ብቻ ተጠቃሚ በሚያደርግ ሥርዓት ውስጥ እንደነበሩ በመጥቀስ፤ የላይኞቹ በተለይም ኢትዮጵያ ለዓባይ ከፍተኛ ውኃ አስተዋፅዖ እያደረገች እንዳትጠቀም ሲደረግ መቆየቱን አንስተዋል። አሁን ላይ ስምምነቱ ወደ ሕጋዊ ተፈጻሚነት መሸጋገሩ የነበረውን ሥርዓት በትልቁ ቀይሮ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሁሉም እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ገልጸዋል።

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ እንዲዘጋጅና በተፋሰሱ ሀገራት እንዲፈረም ኢትዮጵያ በርካታ ጥረት ስታደርግ መቆየቷን ጠቅሰው፣ ስምምነቱ አሁን ላይ ብዙ ደረጃዎችን አልፎ ወደ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ላይ መድረሱ ትልቅ ስኬት መሆኑን አስታውቀዋል።

የማዕቀፉ ስምምነት ዓላማ ማንንም ለመጉዳት አይደለም ያሉት ሚኒስትሩ፣ በተለይ ኢትዮጵያ ስታራምድ የነበረውን በእኩልና በፍትሐዊነት የመጠቀም መብትን የሚያረጋግጥ መሆኑን ገልጸዋል። ሕጋዊ ተፈጻሚነት ላይ መድረሱም በትብብርና በጋራ ለመልማት እንዲሁም የተፋሰሱን ሀገራት ዜጎች እኩል ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ስምምነቱን ያልፈረሙ ለዜጎቻቸው ተጠቃሚነት ወደ ማዕቀፉ መቀላቀል እንዳለባቸውም ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ዛሬ ስኬቱ ሲመጣ ትላንት የነበሩት ብዙ ዋጋ ከፍለውበታል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ የተጀመሩ ሥራዎችን ማስቀጠል ልማዷ መሆኗን ጠቅሰው፤ ስምምነቱ በተጀመረበት ወቅት ትልቅ ሚና የነበራቸውን መሪዎችም አመስግነዋል።

## “የሀገርን ክብር ከፍ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሃገርን ክብር ይበልጥ ከፍ ለማድረግ ማንኛውም ዜጋ በተሠማራበት ሙያ ሁሉ መትጋት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ወርቃማ ክብሯን እንደጠበቀች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንድትሻገር ማድረግ ከእኛ የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እልፍ አዕላፍ ጀግኖች መስዋዕት የሆኑላትን የሉዓላዊነትና የነፃነት ምልክት የሆነችውን ሰንደቅ ዓላማችንን፣ በብሔራዊ የአርበኝነት መንፈስ መጠበቅና መንከባከብ እንደሚገባም አስረድተዋል።

ድላችን፣ ክብራችን፣ አይበገሬነታችን እና በፈተናዎች መካከል ፀንተን መቆማችን በሰንደቅ ዓላማችን ላይ ታትሞ ይኖራል ያሉት አቶ አደም፤ እስከ ፍጻሜው ኢትዮጵያ በልጆቿ ላብና ደም አምራ፣ ደምቃ፣ ፈክታና በልፅጋ ትኖራለች ብለዋል።

ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ክብረ በዓል ማለት የኢትዮጵያን ክብር በዓለም አቀፍ አደባባይ ከፍ ላደረጉ ተገቢውን ክብር መስጠት መሆኑን ተናግረዋል። ቀኑን የኢትዮጵያን ጀግኖች፣ አንድነታችንን እና ኅብረ ብሔራዊ እሴቶቻችንን በማሰብ በተገቢው መንገድ መከበሩ አግባብ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

በዓሉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚከበሩበት ነው ያሉት የፓርቲው ምክትል ፕሬዚዳንት፤ ቀኑን አክብሮ ከማለፍ በተጨማሪ በማንኛውም ጊዜ በተሠማራንበት ሙያ ውጤታማ በመሆን በዓለም አደባባይ ሰንደቃችንን ከፍ ለማድረግ መጣር ይኖርብናል ብለዋል።

በተጨማሪ የሰንደቅ ዓላማ ክብርን፣ ቀለማቱና ምልክቱ ያላቸውን ትርጉም ለትውልድ ማሳወቅ እንደሚገባ አጽንዖት ሰጥተው፤ ሀገር ተረካቢው ወጣት የሰንደቅ ዓላማ አጠቃቀምና ሥርዓትን ጠንቅቆ እንዲያውቅ መሥራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

ለሀገራቸው መስዋዕትነት የከፈሉ ዜጎችን በማሰብ ለኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተከፈለውን ውድ ዋጋ በማስተማር ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ሰንደቅ ዓላማ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የአብሮነታችን ምልክት በመሆኑ፤ አሰባሳቢ መገለጫ የሆነውን ሰንደቅ ማክበር ግዴታ መሆኑን አንስተዋል።

ለሰንደቅ ዓላማ ተገቢውን ክብር መስጠት የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነት ለማስጠበቅ ውድ ዋጋ ለሚከፍሉ ቀደምት ጀግኖች አርበኞችን እና የፀጥታ አካላትን ዕውቅና መስጠት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያን ዕድገትና ብልፅግና እውን ለማድረግ የሚተጉ ብርቱ ክንዶችን ማክበርም የሀገር ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማን የማክበር መገለጫ መሆኑን አንስተዋል።

## የንግድ ማጭበርበርን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እያከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ በኢንተለጀንስ ቁጥጥር፣ በድንገተኛ ፍተሻ፣ በኦዲት፣ በመደበኛ ፍተሻና ሰነድ ምርመራ እንዲሁም የቀረጥ ነፃ መብትን አላግባብ በመጠቀም የንግድ ማጭበርበርን ለመከላከል ቁጥጥር እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ተቋሙ ኮንትሮባንድና ሕገወጥ ንግድን መከላከልና መቆጣጠር ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን አንስተው፤ በሩብ ዓመቱ ሦስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው የወጪና ገቢ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች መያዛቸውን አስታውቀዋል፡፡

በዚህም ሁለት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ግምት ያላቸው ገቢ እቃዎች እና 842 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ግምት ያላቸው ወጪ እቃዎች ተይዘዋል ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ኮሚሽኑ በሩብ ዓመቱ 87 ቢሊዮን 270 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 88 ቢሊዮን 100 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ መቻሉን ገልጸዋል።

አፈጻጸሙ የእቅዱን 100 ነጥብ 8 በመቶ መሆኑን ጠቁመው፤ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ38 ቢሊዮን 450 ሚሊዮን ብር ብልጫ እንዳለው አስታውቀዋል።

ኮሚሽኑ ካሉት ኃላፊነቶች ሌላኛው የተሳለጠ የንግድ አገልግሎት መስጠት ነው ያሉት ኮሚሽር ደበሌ፤ በሩብ ዓመቱ 34 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ግምት ላላቸው እቃዎች የቀረጥ ነፃ መብት አገልግሎት ተሰጥቷል ብለዋል፡፡ ወጪ ንግድን ለማሳለጥና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትም የ24 ሰዓት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን አንስተዋል፡፡

የተቋሙ የሩብ ዓመት አፈጻጸም ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት መሆኑን አመላክተው፤ ለውጤቱ መገኘት በየደረጃው ያሉ ሠራተኞች፣ ግብር ከፋዮች፣ የጉምሩክ አስተላላፊዎችና አመራሮች ጠንካራ ቅንጅት ወሳኝ ሚና እንደነበረው ተናግረዋል።

አፈጻጸሙም ለቀጣይ ሥራ ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑንም ኮሚሽሩ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ፍትሐዊነትን ያሰፈነና የቅኝ ግዛት ዘመን አሮጌ ውልን ያስቀረ ስምምነት!

የናይል ውሃን በፍትሐዊነት ለመጠቀም ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ እልህ አስጨራሽ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ጥረቶቻቸው ከፍ ባሉ ፈተናዎች ውስጥ አልፈው ዛሬ ላይ ታሪካዊ የተባለ የስኬት ምዕራፍ ላይ ደርሷል፤ የናይል ወንዝ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ወደ ትግበራ ተሸጋግሯል ።

የናይል ወንዝ ውሃ የተፋሰሱ ሀገራት ሕዝቦች የጋራ ሀብት ነው፤ ይህን ሀብት በፍትሐዊነት ለመጠቀም የሚደረግ የትኛውም አይነት ጥረት በዓለም አቀፍ ሕግ የሚደገፍ እና የሚበረታታ ነው። ይህም ሆኖ ግን አንዳንድ የተፋሰሱ ሀገራት ሲያራምዱት ከነበረው፤ የብቻ ተጠቃሚነት ፍላጎት አኳያ የወንዙ ውሃ የግጭት እና ያለመተማመን ምንጭ በመሆን የተፋሰሱ ሀገራት ሕዝቦች ቤተሰብነትን ሲፈታተን ቆይቷል ።

በተለይም የቅኝ ግዛት ስምምነቶችን እንደ አስገዳጅ ሕግ አድርገው ለማየት የሚሞክሩት የግብፅ መንግሥታት፤ በተለያዩ ወቅቶች በወንዙ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የሚያነሷቸው ፍትሐዊነት የጎደላቸው ጥያቄዎች፤ ከሁሉም በላይ አፍሪካውያን ለነፃነታቸው ያደረጉትን የመስዋዕትነት ትግል ብቻ ሳይሆን በትግሉ ያገኙትን ድል የሚያሳንሱ ናቸው።

እነዚህ ሀገራት በአንድ በኩል አፍሪካውያን በጋራ ተቋማቸው/ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በኩል የትኛውንም የቅኝ ግዛት ስምምነት ውድቅ ማድረጋቸውን ተቀብለው፤ በሌላ በኩል የተፋሰሱን ሀገራት የውሃ ሀብት ባለቤትነት እና የተጠቃሚነት መብት የሚጻረር ስምምነቶችን ለመተግበር ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል።

ይህ ያልተገባ ዘመኑን የማይዋጅ የወንዙን ውሃ የብቻ ባለቤትነት/ተጠቃሚነት ጥያቄ፤ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በተፋሰሱ ሀገራት ሕዝቦች መካከል አለመተማመንን ከመፍጠር ጀምሮ፤ በተለይ ግብፅ በተፋሰሱ ሀገራት የውስጥ ጉዳይ ሳይቀር ያልተገባ ጣልቃ ገብነተት እንድትፈጽም፤ በዚህም በሀገራቱ ሕዝቦች መካከል በጠላትነት መፈላለግ እንዲያቆጠቁጥ አድርጋለች፤ እያደረገችም ነው ።

ባለፉት አስር ዓመታት የናይል ውሃ የግጭት እና ያለመግባባት ምክንያት ከመሆን ባለፈ፤ የትብብር እና የጋራ ልማት ምንጭ እንዲሆን ለማስቻል በተደረገው ጥረት ውስጥ የግብፅ መንግሥት፤ ጥረቱ እንዳይሳካ ብዙ ያልተገቡ መንገዶችን መርጦ ሲጓዝ ቆይቷል፤ ለፍትሐዊነት ብቻ ሳይሆን የወንዙ ውሀ በተፋሰሱ ሀገራት መካከል የፈጠረውን ተፈጥሯዊ ወንድማማችነት በሚያሳንስ መንገድ ሲንቀሳቀስ ተስተውሏል።

የናይል ውሃን የተፋሰሱ ሀገራት በኃላፊነት እና በፍትሐዊነት መጠቀም ከቻሉ ለሀገራቱ ሕዝቦች ትልቅ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ እንደሚኖረው ይታመናል። ሕዝቦቹን የበለጠ በማቀራረብ የጋራ ተጠቃሚነትን መፍጠር ያስችላል። የደበዘዘውን ወንድማማችነት በማድመቅም የሚኖረው አስተዋፅዖ መተኪያ የሌለው ነው።

ፍትሐዊነት ዓለም አቀፍ መርሕ በሆነበት በዚህ ዘመን፣ የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ ለወለዳቸው ስምምነቶች ትንሳኤ ለመስጠት የሚደረግ የትኛውም አይነት ጥረት፣ በየትኛውም መመዘኛ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይደለም። ዘላቂ የሆነ ጥቅም ያስገኛል ብሎ ማሰብም ለዘመኑ አስተሳሰብ ባዳ መሆን ነው።

ይህ ያልተገባ ጥረት የራስን ሕዝብ አሳስቶ ዋጋ ከማስከፈል የማይዘል እና ሕዝብን እንደ ሕዝብ ላልተገባ የሞራል ስብራት የሚዳርግ ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው። በትናንት ሙት አስተሳሰብ ላይ ቆሞ የማይጨበጥ ተስፋን የመጠበቅ ያህል የሚታሰብ ነው ።

ይህ አይነቱ አስተሳሰብ በቀደሙት ዓመታት፤ በተፋሰሱ ሀገራት ሕዝቦች መካከል የነበረውን ወንድማማችነት ከማቀጨጭ፤ በሀገራቱ ሕዝቦች መካከል አለመተማመንን ከመፍጠር፤ የጋራ ዕጣ ፈንታቸውን የተሻለ ሊያደርጉ የሚያስችሉ ዕድሎች ከማምከን፤ በተለያዩ ሴራዎች ከመደነቃቀፍ ባለፈ በተጨባጭ ተጠቃሚ ያደረገው ሀገር የለም፤ ወደፊትም ሊኖር አይችልም ።

በዚህ ተጨባጭ እውነታ በመነሳት የናይል ወንዝ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን ያልፈረሙ ሀገራት አሁን ላይ ቆም ብለው ከፍትሐዊነት ተጎጂ የሚሆን ማንም ሊኖር እንደማይችል በአግባቡ ሊያስተውሉ ይገባል። በተለይም የተፋሰሱ ሀገራት ሕዝቦች ለፍትሐዊነት ካላቸው ከፍ ያለ ማኅበረሰባዊ እሴት አኳያ፤ ራሳቸውን ዘመኑን በዋጀው አስተሳሰብ ገርተው ስምምነቱን በመፈረም ሕዝባቸውን ዘላቂ ተጠቃሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የወንዙን ውሃ በኃላፊነት መንፈስ በፍትሐዊነት ለመጠቀም የተደረሰበት ስምምነት፤ ትናንት አፍሪካውያን አባቶች ብዙ ዋጋ የከፈሉበት የነፃነት ትግል አንድ አካል ነው። ይህንን እውነታ ለመቀበል ፈቃደኝነት ማጣት የትግሉን አባቶች ውለታ ማሳነስ ፤ የከፈሉትን መስዋዕትነት ትርጉም ማቀጨጭ፤ ከዚያም በላይ አጠቃላይ የሆነውን የቅኝ ግዛት ትግልን ዋጋ ማሳጣት ነው።

አፍሪካውያን ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን የራሳቸውን ዕጣ ፈንታ በጋራ የሚወስኑበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት የቅኝ ግዛት ውሎችን ታቅፎ፤ ከውሎቹ ሙቀት ለማግኘት የሚደረግ ጥረት በዚህ አፍሪካዊ ትውልድ ተቀባይነት የለውም። ይህንን በአግባቡ ማሰብ፤ ለዚህ የሚሆን የፖለቲካ ቁርጠኝነት መፍጠር ስምምነቱን ላልፈረሙ ሀገራት ለነገ የሚባል የቤት ሥራ አይደለም።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የስምምነቱን መፈረም አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት እንዳመለከቱት፤ ሀገራቱ ለፍትሐዊ የውሃ አጠቃቀም በመገዛት “የናይል ቤተሰብን መቀላቀል ይጠበቅባቸዋል“። ለዚህ ደግሞ ከቀደመው ኢ-ፍትሐዊና የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ እና አስተሳሰቡ ከወለደው የተዛባ አካሄድ ራሳቸውን ነፃ ሊያወጡ ይገባል። ይህን ለማድረግና ሕዝባቸውን በፍትሐዊነት መድረክ ከፍ ለማድረግ ከዚህ የሚበልጥ ዕድል መቼም አይኖርም!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## ሰንደቅ ዓላማችን - ለሁለንተናዊ ክብራችን

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

‹‹ሰንደቅ ዓላማ›› የሚለው ስያሜ ከሁለት ቃላቶች አካል የተመሠረተ ትርጓሜን ይዟል።ቃላቶች በተናጠል ሲተረጎሙ ሰንደቅ-ማለት ‹‹ምርኩዝ፣ ምሰሶ፣ በትር እንዲሁም የነፃነትና የሉዓላዊነት ምልክት እንደማለት ነው። ዓላማ ማለት ደግሞ ‹‹ምልክት፣ አቋም፣ ስብ ስብ፣›› የሚለውን ሀሳብ እንደሚያመለክት ለቃሉ የተሰጠው ትርጉሜ ይጠቁማል።

ሁለቱ የቃላት ጥምረቶች ‹‹ሰንደቅ ዓላማ›› በሚል ኅብር በአንድ ይጋመዳሉ። ይህ ማለት ደግሞ የሀገር መታወቂያ፣ የሕዝብ አንድነት መጠበቂያና የክብር መለያ ምልክት እንደማለት ነው። ይህ ታላቅ ስያሜ በሌላ መልኩ ሲቃኝ ሰንደቅ ዓላማ የአንድ ሀገር ሕዝብና መንግሥት ሉዓላዊ ነፃነትና ልዩ ተምሳሌት ሆኖ ይመዘገባል፡፡

ኢትዮጵያ በሰንደቅ ዓላማ ክብር ስማቸውን አድምቀው ጽፈዋል ከሚባሉ ሀገራት ተርታ ትሰለፋለች። ይህ እውነታ ደግሞ ዘመናትን ወደኋላ መለስ ብለን ታሪክን እንድንቃኝ ምክንያት ይሆናል። በሀገራችን ከ1890ዎቹ አጋማሽ ድረስ የነበረው የሰንደቅ ዓላማ ኅብር ወጥነት እንዳልነበረው ይነገራል። ይህ እውነታም ሰማያዊ ነጭና ጥቁር ቀለማት ለዓመታት የባንዲራችን ቋሚ መለያዎች እንደነበሩ የሚጠቁም ነው፡፡

እነዚህ ቀለማት በሰንደቅ ዓላማነት ከመውለ ብለባቸው አስቀድሞም በሀገራችን ጥቅም ላይ የዋሉት ቀለማት መልከ ብዙና ቋሚ ያልነበሩ ናቸው። በዘመኑ ሰንደቅ ዓላማ ማለት ለመንግሥት ግዛት ለሠራዊትና ለሃይማኖት መለያነት ከማገልገል ያለፈ ትርጉም እንዳልነበረው ታሪክ ይጠቁማል።

የዘውዳዊ አገዛዝ ሥርዓት እስኪያበቃ ድረስ የነበሩት ሰንደቅ ዓላማዎች የገዢ መደቦቹን ዓላማ በወከለ መልኩ ምስላቸውን የሚያንፀባርቁ ነበሩ። ይህ መሆኑ ደግሞ ወጥነት ባላቸው ቀለማት ሀገርን የሚወክል ሰንደቅ ዓላማ ዕውን እንዳይሆን ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡

በ1898 ዓ.ም አካባቢ በሀገራችን ለመጀመሪያ በሚባል መልኩ የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት የተለየ ትኩረት አገኙ።ይህ እውነታም አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለማት በኢትዮጵያዊ ማንነት ውስጥ እንዲሰርጹ ልዩ ኃይልን ፈጠረ። አረንጓዴ የልምላሜ፣ ቢጫ የተስፋና ብርሃን፣ ቀይ ደግሞ የመስዋዕትነት ትርጓሜ እንዲኖራቸው ሆኖ ተቀረጸ፡፡

አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ባንዲራ ከፍ ብሎ መውለ ብለቡ ለሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የማንነቱ መሠረት፣ ሊሆን አልዘገየም። ትውልዱ በነዚህ ኅብረ ቀለማት ውስጥ ማንነቱን አጽንቶ ሀገሩንና ዜግነቱን ሊወድ፣ ስለባንዲራው ክብር እስከሕይወት መስዋዕትነት የደረሰ ተጋድሎ ሊያደርግ አቋሙን አጸና። በቀለማቱ ኅብር በትርጓሜው ኃይል ልባቸው በፍቅር የነደደው ወገኖች ባንዲራው ዓላማና ሕይወታቸው ሆነ። ሰንደቅ ዓላማ ማለት ለኢትዮጵያውያን ስምና መለያቸው እስኪሆን ድረስ በክብር ተንበረከኩለት፡፡

በየዘመናቱ በነበሩ አገዛዞች እንደ ሥርዓቱ አይነትና ፍላጎት በሰንደቅ ዓላማው ላይ ከፊል ለውጥ ሲደረግ ቆይቷል። እንዲያም ሆኖ ኢትዮጵያዊነትና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ከከፍታው ዝቅ ብሎ አያውቅም።ሁሌም ለአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ያለው ክብር የቀዘቀዘ አይደለም። ከቀድሞ ታሪኮች እውነታዎች ሲመዘዙ ደግሞ ጽናትና ጥንካሬ ልቆ ይታያል።

ከዘመን ድርሳን ወጎችን ስንሰማ ደግሞ ከአንድ አይረሴ እውነታ ያደርሰናል።የዛኔ የባንዲራው ስም በተነሳበት ዓውድ ሁሉ በንቀት ልቆና ረግጦ የሚያልፍ አንዳች ኃይል አልነበረም። በባንዲራው የሚምል፣ የሚማለድ፣ የሚወስን ትውልድ ዕልፍ ነበር። ይህ ትውልድ ሁሌም ሰንደቁን የማሸነፊያ ኃይል አድርጎ ይረታበታል። ‹‹ወድቆ በተነሳው ባንዲራ›› ይሉት ቃል ከአንደበት ከወጣ ንቅንቅ ይሉት የለም።ባንዲራ ታሪክ፣ ባንዲራ ሕይወት፣ ባንዲራ ሀገር ማለት ነውና፡፡

ኢትዮጵያዊነትና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ትስስራቸው ይለያል። ይህ የማንነት መለያ በጦርነት አውድማ የድል ብስራት ነው። ጀግኖች በተሰለፉበት ግንባር ሕይወታቸውን አሳልፈው ይሰጡለታል። ሰንደቅ ዓላማ በሠላም መንደር የሁሉም መኖርና ሕልውና ሆኖ ዘልቋል። በባንዲራው መውለብለብ የማንነት መልክ ይረጋገጣል፣ የዜግነት መብት በግልጽ ይታያል፡፡

በትምህርት ዓለም ተማሪዎች ሰንደቃቸውን እያዩ በክብር ይዘምራሉ። እያንዳንዱ የመዝሙር ስንኝ ትርጉሙ የሚጎላው በከፍታ ልቆ ከሚታየው ባንዲራ ጋር በእኩል ሲውለበለብ ነው። ይህ የትውልድ አደራ የታተመበት፣ የታሪክ ድርሳን ደምቆ የተከተበበት ሰንደቅ ዓላማ የበዛ መስዋዕነት ተከፍሎበታል። ጀግኖች አርበኞች የጠላት ወራሪን የመከቱበት ኃይላቸው ነው። በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ማንነታቸውን የሚገልጹበት ውበታቸው ነው፡፡

ጀግኖች አትሌቶቻችን በዓለም አደባባይ ድል ሲጎናጸፉ የአሸናፊነት ዓርማቸው ሰንደቅ ዓላማቸው እንደሆነ ዘልቋል። ይህ መላው ዓለም በአድናቆት እጁን በአፉ የሚጭንበት፣ ደማቅ ድልን የሚያይበት ዓርማችን ለበርካታ አፍሪካ ሀገራት ጭምር መሠረት ነው። ያለምንም ቅኝ ግዛት በክብር የኖረችው ኢትዮጵያ ቀድማ ያውለበለበችውን አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ከነፃነት እስራታቸው መፈታት ማግስት እንደ ልዩ ገድ የቆጠሩት ሀገራት ቋሚ መለያቸው እንዳደረጉት ዘልቀዋል፡፡

ሰንደቅ ዓላማ ለኢትዮጵያውያን የጋራ ሀብትና በእኩል የመግባቢያ ሰነድ ነው። በማንነቱ ጉልበት ሺዎችን አንበርክኳል።በውበቱ ድምቀት እልፎችን ማርኳል። በውስጡ ያለው የዕንባና ሳቅ ታሪክም የደም መስዋዕትነት የተከፈለበት ነው። ጀግኖች ለባንዲራቸው ፍቅር ሕይወታቸውን ሲሰጡ ቅር ብሏቸው አያውቅም።

ከአፍሪካ አሕጉር አብዛኞቹ የቅኝ ተገዢ ሀገራት በአንድም ይሁን በሌላ የሀገራችንን የሰንደቅ ቀለም ተውሰው እኛን ሊመስሉን ሞክረዋል።በነፃነታቸው ማግስት ድልን የተመኙት አፍሪካውያን ወንድሞቻችን የኢትዮጵያን ባንዲራ ውለታ መቼውንም ቢሆን የሚዘነጉት አይሆንም። ይህ ለማንነታችን ዓርማና መለያ የሆነው ባንዲራችን ዘመናትን ከእኛው ጋር ዘልቋል ወደፊትም እንዲሁ ይቀጥላል፡፡

ኢትዮጵያዊነትና የሰንደቅ ዓላማ ታሪክ ፈጽሞ ተነጣጥለው አያውቁም። የብሔር ብሔረሰቦች ማንነት የተሳሰረው በዚሁ የቀለማት ኅብር ሆኗል። ሰንደቅ ዓላማችን ትውልድ በማንነቱ የራሱን ዐሻራ እንዲያኖር መሠረቱ ነው። ትናንትን ከዛሬና ከነገ ጋር ለማጠንከር የታሪክ መነሻ ሆኗልና።

በሀገራችን ስለባንዲራ ክብር ሲባል በየዓመቱ ቀኑ በትኩረት ተዘክሮ ያልፋል።በራሱ መርሕና መልዕክት የሚከበረው ይህ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በየጊዜው ሲታወስ ታላቅነቱን በሚዘክርና በሚያስታውስ ዝግጅት ነው። ዘንድሮም ለ17ኛ ጊዜ በመላው ኢትዮጵያ የባንዲራ ቀን ተከብሮ ውሏል።

ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም ተከብሮ የዋለው የሰንደቅ ዓላማ ቀን በትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ ተቋማትና መሰል ስፍራዎች ሁሉ ዕለቱን በክብር አስታውሷል። በዚህ ቀን አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ባንዲራችን በኢትዮጵያ ሰማይ ስር በድምቀት ተውለብልቧል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጎልቶ ተሰምቷል፡፡

‹‹ሰንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ከፍታ›› በሚል መሪ ቃል ተከብሮ ውሏል። ዕለቱም በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀሥላሴ የመከላከያ ሠራዊት አባላት፣ አባት አርበኞችና ሌሎች እንግዶች በተገኙበት በድምቀት ተከብሮ አልፏል፡፡

ዘንድሮም ብሔራዊ አንድነታችን፣ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን፣ እንደ ብረት ጠንክሮ ይዘልቅ ዘንድ የሰንደቅ ዓላማችን ሁለንተናዊ ክብር በከፍታ መታየቱ ይቀጥላል፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ሰንደቅ ዓላማችን ለህብረ ብሔራዊ ድላችን

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)**

ሰንደቅ ዓላማ ሀገር ወካይ፣ ሕዝብ ገላጭ የማንነት መልክ እንደሆነ የሚጠፋው አይኖርም:: በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ የተቀለመው ሰንደቅ ዓላማችን ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሶስት ገላጭ እሳቤዎችን ይዞ ከትላንት ወደዛሬ መጥቷል ወደ ነገም ያዘግማል:: ቀይ የጀግንነት፣ የብርታት ተምሳሌት ሆኖ፣ ቢጫ የሰላም፣ የፍቅር ምልክት ሆኖ አረንጓዴን በአረንጓዴና በልምላሜ ከትበን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በሶስት ዘመን ተሻጋሪ ቀለሞች ስር አሳርፈን ብዙ ተጉዘን እነሆ ዛሬ ላይ ደረሰናል::

በየዓመቱ የሚከበረው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ዘንድሮም « ሰንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችን እና ለኢትዮጵያ ከፍታ!» በሚል መሪ ቃል እና መሃላ ለአስራ ሰባተኛ ጊዜ ተከብሯል:: አዲስ ዓመት በገባ ሰሞን የሚከበረው ይህ በዓል ዓመቱን በኢትዮጵያዊ ስሜት፣ በአብሮነትና፣ በወንድማማችነት እንድናሳልፍ እድል የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር የቀድሞ አባቶቻችን ለሀገርና ሕዝብ የከፈሉትን መስዋዕት የምናስብበትም ጭምር ነው::

በመሪ ቃልና በመሀላ መከበሩ ልዩ ድባብን ከማስገኘቱ ጎን ለጎን ለባንዲራ ያለንን ክብር ከፍ እንድናደርግ፣ የተከፈለልንን ዋጋ እንድናውቅ፣ በአብሮነት እንድንጓዝ፣ ቃል ወደተግባር ተቀይሮ ሀገራችንን በልማትና በሰላማዊ መንገድ እንድንመራ እድል የሚሰጥ ነው:: እኛ ኢትዮጵያውያን ብሎ የሚጀምረው የዘንድሮው የሰንደቅ ዓላማ ቀን መሀላ በይዘቱና በቁም ነገሩ ፍሬ ያለው፣ በአንድነት ስለአንድነት እንድንተጋ አጽንኦት የሚሰጥ፣ ኢትዮጵያና ከፍታዋ ላይ ያተኮረ መሆኑ ከቃለ መሃላው መረዳት ይቻላል::

‹እኛ ኢትዮጵያውያን...ድህነትና ኋላቀርነትን አስወግደን፣ ኢትዮጵያችን በልማትና በዲሞክራሲ ጎዳና ውስጥ የሕዝቦችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ትሰለፍ ዘንድ፣ የጀመርነውን የለውጥ ጉዞ ወደማይቀለበስ ደረጃ ለማድረስ፣ በየጊዜው እያጋጠሙን ያሉ ችግሮችን በማስወገድ፣ በአንድነትና በጋራ ስሜት፣ አብሮ በመቆም በየዓመቱ በመንግሥት ትኩረት አግኝተው የታቀዱ የልማትና የመልካም አስተዳደር እቅዶቻችንን ለማሳካት፣ በሀገራችን ሰንደቅ ዓላማ ፊት ቃል እንገባለን› የሚል ነው::

መሀላ እንደ ቃል የእምነት እዳ ነው:: ቃል ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ እንደሚባለው ሀገርኛ ሥነ-ቃል ዋጋው ከፍ ያለ ነው:: ስለሀገር ሲሆን ደግሞ ትርጉሙ ከዚህም በላይ ይገዝፋል:: እኛ ኢትዮጵያውያን ለቃል የተለየ ቦታ የምንሰጥ መሆናችን በብዙ አጋጣሚዎች የታየ እውነታ መሆኑ የሚያጠራጥር እንዳይደለ ብዙ ማረጋገጫዎች አሉ:: ከሁሉም በላቀውና የሁላችንም የክብርና የሉዓላዊነት ቀለም በሆነው ሰንደቅ ዓላማ ፊት ቆመን የገባነው መሀላ ጥልን በፍቅር፣ ክርክርን በውይይት የሚሽር የአብሮነት ስሜትን ከመጫሩ እኩል ለሀገራችን ያለ ነው እኛ እንደሆንን፣ ከእኛ ብርቱ ትስስርና ጉርብትና ሌላ ነፃ አውጪ እንደሌላት የሚጠቁምም ነው::

እንዲህ ባለው ሕዝባዊ መሃላ በመታገዙ እስከ ዛሬ ከተከበሩት የሰንደቅ ዓላማ ቀኖች የዘንድሮው ለየት እንደሚል አምናለሁ:: ለተግባር በሚያተጉ አንቂና አብቂ መሀላዎች ችግሮቻችንን ካልተጋፈጥናቸው አስቸጋሪ የመሆናቸው ነገር ሳይታለም የተፈታ ነው:: በአንድ ዓመታዊ ክብረ-በዓል ወይም ወደፊት ለምንተገብራቸው ሀገራዊ ጉዳዮች አበባ ስናስቀምጥ፣ ሻማ ስናበራ፣ ሪቫን ስንቆርጥ አብረን እንዲህ ያሉ የትጋትና የንቃት መሃላዎችን መጨመራችን አዋጪነቱን የገዘፈ ያደርገዋል::

የቃል ትንሽ፣ የመሃላ መናኛ የለውም:: ሁሉም ቃሎች ከአንደበታችን እስከ ወጡ ድረስ ባለመከበራቸው በፈጣሪና በህሊናችን በኩል ተጠያቂ ሊያደርጉን ኃይል አላቸው:: ቃል ስንገባና መሀላ ስንፈጽም ለዛ ቃልና መሀላ ተገዢ በመሆን ነው:: በዛሬው እለትም የገባነው የመሃላ ቃል የመላው ኢትዮጵያውያን የእምነት እዳ ሆኖ የሚጠራ ነው:: ቃላችንን በማክበር፣ ለሀገራችን በመልፋት፣ ስለአብሮነት ዋጋ በመክፈል፣ ድህነትና ኋላቀርነትን በመፋለም፣ ልማትና ዲሞክራሲ፣ ተጠያቂነትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ጠጠር በማዋጣት መሀላችንን በተግባር ማረጋገጥ አለብን::

> **ባልተንሻፈፈ አቋቋም ቀጥ ብለን ቆመን፣ እጃችንን በትከሻችን አቅጣጫ ያለውልጋዴ ዘርግተን፣ በሥርዓትና በግብረገብነት ስንታይ ያ ዘመን የት ሄደ እንድል ያደርገኛል**

የባንዲራ ቀንን ብቻ አይደለም በሀገርና በማህበረሰብ ስም የሚከበሩ እንደ ዓድዋ፣ እንደ አርበኞች ቀን፣ እንደ ሰማእታት ቀን ያሉ የድል ቀኖችን እንዲህ ባለው መንፈስ በቃልና በመሃላ፣ በብሔራዊ መዝሙርና አንድነትን በሚያጠነክሩ የእርስ በርስ የበጎ እሴት ልውውጥ ብናከብራቸው ጥሩ ውጤት እንደምናመጣ ባለተስፋ ነኝ::

የተለማመድነው በአበባና በሻማ ማብራት ዘክሮ ማለፍ ነው:: ትርጉሙ እንዲገባን፣ ዓላማውን እንድንረዳ፣ ለትውልዱ ያለው ፋይዳ እስከ የት እንደሆነ ለማወቅ ቀለል ብለው ለየት ያሉ የአከባበር ሥነ ሥርዓቶች ዋጋቸው ብዙ እንደሆነ አምናለሁ:: ጥሩ የሆኑና በሀገር ጉዳይ ላይ የጋራ መንፈስን የሚፈጥሩ እንዲህ ያሉ የትስስር ገመዶች ለመቼም እንዳይበጠሱና እንዳይላሉ የጠበቁ ናቸው::

አንዳንድ የልጅነት ጥበቦች አሉ በምንም የማይከለሱ፣ ዘመን ደፍሮ የማይሽራቸው፣ ጊዜ ችሎ የማይደፍራቸው ሁነቶች:: ልጅነት እንደኪታብ ነው በሕይወት በፊር ላይ የሚውል:: አፍላነት እንደ ዶቃ ነው ቅጭልጭልታው እስከ እድሜ ጥግ የሚከተል:: ዛሬም ድረስ አልረሳ ብለው ከወጣትነትና ከጉልምስና ከእርጅናም አፋፍ ያልጠፉ፣ ትናንትናዎችንን ያጣፈጡ የብዙ ትዝታዎች ባለቤቶች ነን:: ከነዚህ ትዝታዎች መሀል አንዱ ደግሞ የሰንደቅ አላማ የአከባበር ትዝታ ነው::

በልጅነቴም ሆነ በአሁኑ የወጣትነት እድሜዬ እንደ ባንዲራ ክብር የተገባው ነገር አይቼ አላውቅም:: ለምን የሚለው ጥያቄ እስከሆነ ልጅነቴ ድረስ መልስ አልባ ነበር:: እየሰነበትኩ ስሄድ ነው እኔን፣ ከመልክና ወዜ ጋር ቀልሞ የያዘ ገጸሰቤ እንደሆነ የተረዳሁት:: በትምህርት ቤት የባንዲራ ደፍ ስር በክብር፣ በሥርዓት፣ በጨዋነት የቆምነው፣ ድምጻችንን አዝልገን ለመቼም ከሆድ በማይጠፋ ህብረ ዝማሬ የተቀኘነው የክብር ወግ ዛሬም መታወሻዬ ነው::

ባልተንሻፈፈ አቋቋም ቀጥ ብለን ቆመን፣ እጃችንን በትከሻችን አቅጣጫ ያለውልጋዴ ዘርግተን፣ በሥርዓትና በግብረገብነት ስንታይ ያ ዘመን የት ሄደ እንድል ያደርገኛል:: በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ፊታውራሪነት ሰልፋችንን አስተካክለን፣ እጆቻችንን ከፊትና ከኋላ በቆሙ ወዳጆቻችን ትከሻ ላጥ ጥለን፣ ስለኢትዮጵያዊነት ያዜምነው፣ ስለ ሀገር ፍቅር የዘመርነው ዝማሬ የሁልጊዜ ናፍቆቴ ነው::

የዜግነት ክብር ስንል በጽኑ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ አንዳንዴም በእንባ ታጅበን የተቀኘነው ፊተኛ ጥበባችን፣ በአንድ ስም፣ ለአንድ አላማ «ኢትዮጵያችን ኩሪ እኛም ባንቺ እንኩራ» ስንል ያስተጋባነው የመንፈስ ከፍታ በዚህ ትውልድ ላይ እንዲያቆጠቁጥ እመኛለሁ:: ልብን ሰቅዞ በሚይዘው ብሔራዊ መዝሙር ታጅበን ባንዲራ ሲወጣና ሲወርድ ከምንሆነው መሆን በላይ ፊታችን ላይ ያለው የስሜት ልህቀት ነበር እጅጉን የሚያስገርመው:: ትላንትን ወደ ዛሬ አምጥቶ ወደ ነገም ማራመድ ቢቻል ያን መንፈስ፣ ያን ማንነት፣ ያን ህብረ ብሔራዊነት፣ ያን ሀገር ፍቅር ስሜት፣ ያን ኢትዮጵያዊነት፣ ያን ወንድማማችነት፣ ያን ትቅቅፍ እመልሰው ነበር:: ርግጥ እንደ በፊቱ አይሁን እንጂ ያን መሳይ መልክ አሁንም አለ::

አንዳንድ ስጦታዎች የሕይወት ዘመን ሀብቶች ያህል ናቸው:: ሀገር ለሕዝብ፣ ሕዝብ ለትውልድ ሊሰጡት የሚገባ ትልቁ ስጦታ ወንድማማችነትን ነው:: አባቶቻችን በሀገር ፍቅር ስሜት ለባንዲራቸው ሞተው አንድነትን፣ ወንድማማችነትን፣ ኢትዮጵያዊነትን ከነፃነትና ከሉዓላዊነት ጋር ሰጥተነዋል:: ይሄ በምንም የማይመነዘር፣ ከፊተኞቻችን የተቀበልነው፣ ለውድድር ሚዛን ላይ የማይወጣ ለእያንዳንዳችን ድንቅ ስጦታችን ነው:: እኛም እንደ ፊተኞቻችን ሁሉ ለኋለኞቻችን ልንሰጠው የሚገባ እንደ ፍቅርና፣ ይቅርታን የመሰሉ ነፃ አውጪ መርሆች ሊኖሩን ግድ ይላል::

ተሰጥቶን ሀገርና ሕዝብ ሆነናል:: ተሰጥቶን ባለታሪክና ፊተኞች ተብለናል:: እንደተቀበልነው ሁሉ ለሚመጣው የምንሰጠው የመልካም እሴት ዋጋ ሊኖረን ይገባል:: መጪው ትውልድ ባለፈው እንዳይጠራ የራሳችንን ጀብድ ልናስቀምጥለት እንደ ዜጋ ግዴታ አለብን:: የሰንደቅ ዓላማ ቀን መከበር ትርጉሙም ይሄ ነው:: የተቀበልነውን በመስጠት እና ተንከባክቦ በማኖር ትውልድ መፍጠር፣ ሀገር ማስቀጠል ላይ ያተኮረ ነው::

ሀገር ማለት ባንዲራ ናት:: ሕዝብ፣ ትውልድ፣ ታሪክ፣ ቅርስና ማንነት በዚህ ሰንደቅ ዓላማ በኩል ነፍስ የዘሩ ናቸው:: ትላንት ዛሬና ነገ ሳይቀሩ የነበር ትውስታቸውን ሽረው ውዳዴን የሚያሳዩት እንዲህ ባለው ክብረ በዓል እለት ነው:: መቶ ሃያ ሚሊዮን ሕዝብ፣ ከበዛና ከገዘፈ ህብረ ብሔራዊነቱ ጋር፣ ከወግና ልማዱ እንዲሁም ከማንነቱ ጋር በዓለም አደባባይ የሚታየው በወከለው ሰንደቅ ዓላማው በኩል ነው:: ራስን በኳለ ሁኔታ ብዙኅነት ከነሙሉ ክብሩ ማንነቱን የሚገልጥበት ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙርን የመሳሰሉ ከሕዝብ መንጭተው ሕዝብን የሚያረሰርሱ የጋራ ታሪኮች እንደ በጎ ማህበራዊ እሴቶች የሚወሰዱ ናቸው::

በፖለቲካው ምህዳር ትልቁ የሥልጣን እርከን ባንዲራ ነው:: ቀላል ይመስላል አይደል? ቀላል ግን አይደለም:: ባንዲራ ስላችሁ ጨርቁን እያልኩ አይደለም:: ከጨርቁና ከቀለሙ ባሻገር ስላለው ታላቅ እውነታ መናገሬ ነው:: ስለወከለው ሕዝብና ስለቆመለት ዓላማ፣ በሞትና ሕይወት ኑባሬ ስር ስለቆመ የቃል ኪዳን አደራ ማውራቴ ነው:: ኢትዮጵያዊነትን ስለሳለው፣ ብዙኅነትን ስላቀፈው፣ ትናንትን ከዛሬና ከነገ ጋር ስላስተሳሰረው ገድሉ መናገሬ ነው:: የሶስት ሺ ዘመንን የታሪክና የሥልጣኔ፣ የክብርና የሉዓላዊነት፣ የፍትህና የነፃነት ብኩርናን ማለቴ ነው::

በአጭር ቃል የባንዲራን ግዝፈት ለመረዳት ሀገርና ሕዝብ ያሉበትን ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ሁነት መመልከት ብቻ በቂ ነው:: በትላልቅ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች፣ ክብርና ማንነት በሚንጸባረቅባቸው በየትኞቹም ሁነቶች ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ የሚውለበለበው ሰንደቅ ዓላማችን ነው:: በፖለቲካው ዓለም በሹም ሽረት ወቅት የሚደረግ የሥልጣን ርክክብ እንኳን ባንዲራ ሰጥቶ በመቀበል ይሁንታ የሚያገኝ ነው:: ታላቅ ትርጉም ባላቸው የፖለቲካ ጫፎች ላይ በከፍታና በዝቅታ ተሰቅሎ የሕዝብን ስሜት ከመግለጽ አኳያም ሚናው የላቀ ነው::

በእውነቱ ከያዘው የሶስት ቀለም ንድፍና ከገባን ውስን ትርጉሙ በቀር ስለ ሰንደቅ ዓላማ የገባን አይመስለኝም:: ሰንደቅ ዓላማ የኢትዮጵያዊነት ሌላኛ ስሙ ነው:: እኔን ከሌላው፣ ሌላውንም ከኔ ጋር አመሳስሎ ኢትዮጵያዊ የሚል የጋራ ስም ያገኘንበት የክብር ጌጣችን ነው:: ባንዲራን ማወቅ ሀገርን ማወቅ ነው:: ሰንደቅ ዓላማን መረዳት ኢትዮጵያዊነትን መረዳት ነው:: አባቶቻችን ለባንዲራ ተዋደቁ ስንል ለሀገርና ሕዝብ ተዋደቁ እያልን መሆኑ የሚያሻማ ባይሆንም የመጨረሻው የእውነት ጥግ ግን ለህብረ ብሔራዊነት ዋጋ መስጠት የሚለው ነው::

ንቁ ትውልድ በሌሎች ሀገራት ተጽዕኖ ሳይሆን አባቶቹ ባስቀመጡለት በራሱ እሴት በኩል የሚፈጠር ነው:: የተሰጠንና አባቶቻችን ያስቀመጡልን ደግሞ ከጥላቻና ከዘረኝነት የራቀ፣ ስለሌላው ግድ የሚለውን ኢትዮጵያዊ ማንነት ነው:: ባንዲራ በሚለው ስም በኩል ከፊተኞቻችን የተሰጠን የክብርና የታላቅነት ቀለም አለ:: የተሰጠንን ከዚህም ከዚያም ከምንሰማው አሉባልታ ጋር እያመዛዘንን ውለታ በል እየሆንን ያለን ጥቂቶች አይደለንም:: ከሁሉም የሚበልጥ እውነት ቢኖረን በሰንደቅ ዓላማ በኩል የሚገለጥ ሀገራችን እና ሕዝባችን ነው::

ሰንደቅ ዓላማችን ህብረ ብሔራዊ ድላችን ሆኖ ብዙ ሰንብቷል:: ነፃነትና እኩልነት፣ ጀግንነትና ሉዓላዊነት መልካቸውን የተዋበች፣ የቆራጥ ስም ማንነት ቀለም ነው:: ኢትዮጵያዊ ስንሆንና ስንባል በዚህ የሶስትዮሽ ቀለም በኩል ተንጸባርቀን ነው:: ቃላችንን ወደተግባር፣ መሀላችንን ወደእውነታ በመቀየር እንደ መንግሥትና እንደ ዜጋ ኃላፊነታችንን በመወጣት አጋርነታችንን ማሳየት ከሁላችን ይጠበቃል::

የሀገር ፍቅር መገለጫ ከሆኑት ውስጥ ቃልን ማክበር እና መሀላን መፈጸም ዋነኞቹ ናቸው:: ምናልባት እንደ ሀገር የከሰርንባቸውንና አልመን ያልደረስንባቸውን አንዳንድ ትልሞቻችንን መለስ ብለን ካስተዋልን ከቃል የዘለለ ምንም ነገር አለማድረጋችን በቀዳሚነት የሚነሳ እውነታ ይሆናል:: ካለፈው ተምረን ሰንደቅ ዓላማችን ፊት፣ ስለሀገራችን፣ ስለነጋችን የገባነውን መሀላ በመፈጸም የተሻለ እምርታ ማሳየት እንዳለብን በመጠቆም ላብቃ:: ቸር ሰንብቱ::

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የማዕከላቱ የሮቦቲክ ቴክኖሎጂ ውድድር

ወርቅነሽ ደምሰው

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በርካታ የዓለም ሀገራት በሮቦቲክ ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት አድርገው እየሰሩ ናቸው:: በዚህ የሮቦቲክ ቴክኖሎጂ ላይ በርካታ ተግባሮች እየተከናወኑ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሮቦቲክ ኦሊምፒያድ ውድድር ይካሄዳል፤ ይህ ውድድር እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2004 የተጀመረ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም ጨምሮ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት በውድድር ሲሳተፉ አይስተዋልም:: ዘንድሮ ግን ኢትዮጵያ ጨምሮ ሦስት የአፍሪካ ሀገራት የመሳተፍ እድሉን አግኝተዋል::

በዚህ ውድድር ለመሳተፍ ይቻል ዘንድ በሀገሪቱ በሚንቀሳቀሱና ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ፣ አርትና ሂሳብ ላይ አተኩረው በሚሰሩት ስቲም ማዕከላት አማካይነት በርካታ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል:: ባለፈው ሳምንትም በዓለም አቀፍ ውድድር ኢትዮጵያን በመወከል የሚሳተፈውን የሮቦቲክ የፈጠራ ውጤት ቡድን ለመለየት የሚያስችል የውድድር መርሃ ግብር በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተካሄዷል::

ዶክተር ስሜነው ቀስቅስ የስቲም ፓውር ድርጅት የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ናቸው:: እሳቸው እንደሚሉት፤ ስቲም ፓውር በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር የተዘጋጀ ነው:: በውድድሩ ለሚሳተፉ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች በሚገኙ 40 የስቲም ፓውር ማዕከላት ተማሪዎች ላለፉት ሁለት ወራት ስልጠናዎች ወስደዋል፤ በዚህም ለዓለም አቀፉ ሮቦት ኦሎምፒያድ የሚመረጠው አሸናፊ ተለይቷል::

ከ600 በላይ የሚሆኑ ከሁለተኛ ደረጃና ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተወጣጡ ተማሪዎች በማዕከላቱ ሲሰለጥኑ የቆዩ ሲሆን፣ ተማሪዎቹ የሰሯቸውን ሮቦቶች በእዚህ መድረክ አቅርበዋል:: መድረኩ ሮቦቶቹ የሰውን ፣ የአካባቢን እና የማህበረሰብን ችግር የመፍታት አቅማቸውን መነሻ በማድረግ ተገምግመው በዓለም አቀፍ ደረጃ በተቀመጡ ዳኞች አማካኝነት ተገምግመው በኅዳር ወር በቱርክ በሚካሄደው ዓለም አቀፍ ውድድር ኢትዮጵያን የሚወክለው ተሳታፊ ተለይቶበታል::

በፕሮጀክቶቹ ሁለት ወይም ሦስት እና ከዚያ በላይ ተማሪዎች ተሳትፈዋል:: ውድድሩ ከተለያዩ ተቋማት 37 የሚሆኑ የሮቦቲክስ ቴክኖሎጂዎች ቀርበውበታል:: ስልጠናው በ40 ማዕከላት የተሰጠ ቢሆንም፣ በተለያዩ ምክንያቶች ሁሉም ውድድሩ ላይ መሳተፍ አልቻሉም:: እነዚህ 37 ፕሮጀክቶች ከአዲስ አበባና ከሁሉም ክልሎች የመጡ ናቸው::

ዶክተር ስሜነው እንዳብራሩት፤ ስቲም ፓውር በኢትዮጵያ 65 ማዕከላት አሉት፤ በእነዚህ ማዕከላት በሮቦቲክስ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኮምፒዩተር ሳይንስ፣ በሌሎችም መሰረታዊ ሳይንስ በሚባሉት በሂሳብ፣ በፊዚክስና በሌሎችም ዘርፎች ስልጠናዎች ይሰጣሉ:: ሰልጠናውን ያገኙ ተማሪዎችም በሚቀጥለው ወር በሀገር አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ ለዘጠነኛ ጊዜ በሚካሄደው ሀገር አቀፍ የሳይንስና ኢንጂነሪንግ መድረክ ሥራዎቻቸውን ያቀርባሉ:: የዘንድሮ ፕሮግራም ቀደም ካሉት ስምንት ፕሮግራሞች ለየት ባለ መልኩ ሮቦቲክስ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው::

ከቀረቡት ፕሮጀክቶች ያሸነፈው አንድ ፕሮጀክት ብቻ ኢትዮጵያን ወክሎ ቱርክ በሚካሄደው ውድድር ላይ ይሳተፋል የሚሉት ዶክተር ስሜነው፤ ዓለም አቀፉ የሮቦት ኦሎምፒክ በውድድሩ ላይ እንዲሳተፉ እድሉን ከሰጣቸው አራት የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነች ይገልጻሉ::

‹‹ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር የምትሳተፈው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፤ እንድትመረጥ ካደረጓት ምክንያቶች መካከል እንደ ሀገር ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግና ሂሳብ ትምህርት ዙሪያ ስቲም ፓውር ባከናወነው ተግባር ነው:: ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በእነዚህ መስኮች መሥራት ከጀመረ 15 ዓመታትን አስቆጥሯል:: በእ.ኤ.አ 2020 ጀምሮ ለሌሎች ሀገራት የእኛ ሀገር ተሞክሮ ማጋራት ጀምረናል:: ደቡብ ሱዳን፣ ሩዋንዳ የመሳሰሉ 33 የአፍሪካ ሀገራት አድርሰናል:: ስቲም ፓውር ሮቦቲክስ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራት ከጀመረ ስምንት ዓመታት ተቆጥረዋል:: የሮቦቲክስ ወደ ዓለም አቀፍ መድረክ ለማድረስ ግን እድሉ አልነበረም:: ይህም የሆነበት አቅም ሳይኖር ቀርቶ ሳይሆን የፋይናንስና የሎጂስቲክ የመሳሳሉ ችግሮች ስለነበሩ ነው:: አሁን ከዓለም አቀፍ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ ስለተደረገ ኢትዮጵያን ወክሎ በውድድሩ ላይ መሳተፍ ተችሏል›› ይላሉ ::




የኮተቤው ስቲም ፓወር ማዕከል በቱርኩ ውድድር ለመሳተፍ አሸናፊ ሆኗል



በውድድሩ አንደኛ በመውጣት በቱርክ የሚሳተፈው ቡድን የሰራው ‹‹አዳብቴብል ሮቦት››

እሳቸው እንደሚሉት፤ እያንዳንዱ ስቲም ማዕከል የሰልጠናቸውን ተማሪዎች በተናጠልና በቡድን በማድረግ በሮቦቲክስ ቴክኖሎጂ የተለያየ የአካባቢዎች ችግሮችን መፍታት የሚችሉ ፕሮጀክቶችን እንዲሰሩ አቅጣጫ ተሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል:: የመመዘኛ መስፈርቱን አሟልተው ለመጨረሻው የደረሱት ፕሮጀክቶች እያንዳንዳቸው የሦስት ደቂቃ ቪዲዮ ሰርተው ለዳኞች እንዲልኩ ተደርጓል:: ከተላኩት ቪዲዮች መካከል ለዓለም መድረክ ሊመጥኑ የሚችሉት ፕሮጀክቶች ተመርጠው ለውድድር ቀርበዋል::

ከተሰሩት ሮቦቶች አንዳንዶቹ በግብርና ዘርፍ ሌሎቹ ደግሞ በጤና ዘርፍ እንዲሁም ደንገተኛ አደጋ ሲከሰት ሰው የማይደርስባቸው ቦታዎች ድረስ ደርሰው ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው:: እነዚህ ደግሞ የዕለት ተዕለት ኑሮአችን ላይ የራሳቸው ሚና አላቸው:: ከዚህ ባለፈ በቀጣይ በሰው ሠራሽ አስተውሎትና ሌሎች የቴክኖሎጂ ግኝቶች ሥራ መሠረት ይሆናሉ:: በሌላ በኩልም በኢትዮጵያ እየተካሄደ ላለው የ5ሚሊዮን ኮደሮች ስልጠናም አንዱ መሠረት ሊሆን ይችላል::

ለተማሪዎቹ የተሰጠው ሰልጠና ከስልጠናም አልፎ መተግበር ላይ የደረሰ እንደመሆኑ በዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ላይ የራሱ ዐሻራ ይኖረዋል ያሉት ዶክተር ስሜነው፣ በቀጣይም በትክክል የአካባቢን ችግር በተለያየ ዘርፍ የሚፈታና የሚተገበር ከሆነ በብዛት ተመርቶ ወደ ገበያ እንዲገባና ወደ ሀብት ፈጠራ እንዲሄድ ለማድረግ ታቅዷል::

ከእነዚህ 37 ፕሮጀክቶች ውስጥ አሸናፊው ኢትዮጵያን ወክሎ ወደ ውጭ ሀገር ይሄድ እንጂ ሁሉም አሸናፊዎች ናቸው ያሉት ዶክተር ስሜነው ፤ ‹‹ስቲም ፓውር ፍብሪኬሽን ላብራቶሪና የተሟሉ ማሽኖች ያሉት በመሆኑ በቴክኒክና በፋይናንስ ድጋፍ ተደርጎላቸው ለገበያ እስኪቀርቡ ድረስ ክትትልና ድጋፍ ይደርግላቸዋል›› ሲሉ ገልጸዋል::

በውድድሩ ተማሪ በረከት አሰፋና ጓደኞቹ ከኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ስቲም ማዕከል ‹‹አዳብቴብል ሮቦት›› የተሰኘ የፈጠራ ሥራ ይዘው ቀርበዋል:: ሮቦቱ በተለያዩ ዘርፍ በግብርና ፣ጤና ፣ በኢንዱስትሪ የተለያዩ ሥራዎች መሥራት የሚያግዝ እንደሆነም ተናግረዋል:: እነ ተማሪ በረከት ማዕከሉ ከተቀላቀሉ ሁለት ዓመታት እንደሆናቸው ተማሪ በረከት ይናገራል፤ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የፈጠራ ክህሎትና አቅም ያላቸው ተማሪዎችን አሰባሰቦ ለአንድ ዓመት ያህል ስልጠናዎች (በሀርድዌር፣ ሶፍትዌር፣ የተለያዩ የሮቦቲክስ እና ሲስተሞችን በተመለከተ) መውሰዳቸውን ይናገራል::

እነ ተማሪ በረከት ‹‹አዳብቴብል›› የተሰኘውን ሮቦት ለአምስት ሆነው ሰርተው ነው ለውድድር ያቀረቡት:: ሮቦቱን ለመሥራት ያነሳሳቸው እንደ አፍሪካ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ የሚደረገው አስተዋጽኦ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ነው:: ይህን አስተዋጽኦ ሊጨምሩ የሚችሉ ነገሮች መኖር እንዳለባቸው በማመን ወደዚህ ሮቦት መሥራት ገብተዋል::

ተማሪ በረከት እንደሚለው፤ ሮቦቷ ከወዳደቁ ቁሶች የተሰራች ናት:: 3ዲ ዲዛይን በመጠቀም ለሮቦቷ የሚያስፈልጉ ቁሶችም እዚሁ ነው የተሰሩት:: በአጠቃላይ ሮቦቷ የተሰራባቸው ቁሳቁስ በሀገር ውስጥ በቀላሉ የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን ዋጋቸውም በጣም ዝቅተኛ ነው:: ሮቦቷ ሰው ሠራሽ አስተውሎት ስላለት በራሷ ውሳኔዎች ዋና ዋና ሥራዎችን ትሰራለች፤ ኃይል ቆጣቢም ናት:: ከሰባት በላይ በሚሆኑ ዘርፎች ላይ አገልግሎት መስጠት የምትችልና የተለያዩ ሮቦቶች ሊሰሩ የሚችሉትን በአንድ ላይ አድርጋ መሥራት ትችላለች::

‹‹ሮቦቷ ያለ ማቋረጥ ዓመቱን ሙሉ መሥራት ትችላለች›› የሚለው ተማሪ በረከት፤ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳላትም ይገልጻል:: አንደኛ በኢንዱስትሪው ላይ ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ለመሙላት ትረዳለች:: ለሥራው የሚያስፈልገውን የኃይል መጠንም በጣም ትቀንሳለች:: ሁለተኛ በራሷ ኃይል ቻርጅ እያደረገች ተመልሳ ሥራዋን መቀጠል ትችላለች:: በሦስተኛነት በኢንዱስትሪዎች የሚሰጧትን ማንኛቸውንም ዓይነት ሥራዎችም መከናወን ትችላለች::

ተማሪ በረከት ሃሳብ ብዙ ነገሮች ለማከናወን የምታስችለው ሮቦት ተከታታይ ማሻሻያ እንደሚደረግባት ተናግሯል:: ይህ ሲሆን ሮቦቷ በኢትዮጵያ ሆነ በአፍሪካ ደረጃ በማኑፋክቸሪንግ ወይም በግብርና ዘርፍ የተለያዩ አስተዋጽኦ እንድታበረከት ማድረግ እንደሚቻል ጠቁሟል:: ሮቦቷ የተሰራችበትን መንገድ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ክፍት በማድረግም ሮቦቷን በተለያዩ መንገዶች እያሻሻሉ እንዲጠቀሙ ለማድረግ መታሰቡንም ተናግሯል:: ይቺኛዋን ሮቦት ከኢንቬስተሮች ጋር በመነጋገር ሊጨመሩ የሚችሉ አዳዲስ ነገሮች በመጨመር ለተለያዩ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ተግባራዊ እንድትሆን አቅደው እንደሚሰሩም ይገልጻል::

ሌላኛው የውድድሩ ተሳታፊ እነ ተማሪ መህናየም ተሻገር እና ጓደኞቿ ናቸው፤ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ ስቲም ማዕከል የመጡ ናቸው:: እነሱም የሚወዳደሩበትን ፕሮጀክት ይዘው ቀርበዋል:: ማዕከሉን ከሁለት ዓመት በፊት የተቀላቀሉት እነ ተማሪ መህናየም፣ ማዕከሉን ከመቀላቀላቸው በፊት ያላቸው ውስን እውቀት ነበር፤ ይህንንም በስልጠና በማሳደግ የሮቦት ቴክኖሎጂ መሥራት ችለዋል::

ለአካባቢና ለአጠቃቀም ምቹ የሆነች፣ ቆሻሻ የምትሰበስብና የምታሰወግድ ሮቦት ሰርተው ነው ለውድድሩ የቀረቡት:: የፈጠራ ሥራውን ለመሥራት ያነሳሳቸው ቆሻሻ የሚሰበሰብበትና የሚወገድበት ሂደት ለማዘመን ማሰብ ነው:: አሁን ባለው የሀገሪቱ አሰራር ቆሻሻን ለማንሳት ጥቅም ላይ የሚውለው የሰው ጉልበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህን የኢትዮጵያ ችግር ብቻ ያልሆነና ዓለም አቀፍ የሆነን ችግር ለመፍታት የሚችል ሮቦት መሥራታቸውን ይገልጻሉ::

የእነ ተማሪ መህናየም ቡድን ሦስት አባላትን ያቀፈ ነው:: ሮቦቱን ለመሥራት ሶፍትዌር እና ሀርድ ዌር ቴክኖሎጂዎችን መሥራታቸውን ይናገራሉ:: ከሶፍትዌር መካከል የራሳቸው ዌብ ሳይት እና አንድሮይድ መተግበሪያ ሰርተዋል:: ሮቦቷን እንደ አስፈላጊነቱ በስልክ ማዘዝ የሚያስችል ኤም አይቲ የተሰኘ መተግበሪያም እንዲሁ ሰርተዋል:: በሀርድ ዌር በኩልም ብዙ ቁሳቁስ በመጠቀም ነው ሮቦቷን የሰሩት:: አሁን ሮቦቷ በሰው ሳይሆን ራሷን በራሷ መመራት የምትችል መሆኗንም ተማሪ መህናየም ትገልጻለች::

ተማሪ መህናየም እንደምትለው፤ ሮቦቷ በባትሪ የምትሰራ ሲሆን፤ ወደፊት ግን ሶላር ኢነርጂን መጠቀም እንድትችል ለማድረግ ታቅዷል:: ማሻሻል እንድትችል ተደርጋ ዲዛይን የተደረገች ናት:: አሁን በፕሮቶታይፕ ደረጃ ትሰራ እንጂ ወደፊት ድጋፍ ማግኘት ከተቻለ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ተግባራዊ መሆን እንድትችል ተደርጋ መሥራት ትችላለች::

ቆሻሻዎች የምትሰበስብ ብቻ አይደለችም፤ የተሰበሰበውን ቆሻሻ በየዓይነቱ በመለየት ማስቀመጥ ትችላለች:: ይቺ ሮቦት ተግባር ላይ ስትውል ቆሻሻ የመሰብሰቡን ሥራ ሙሉ በሙሉ በራሷ ያለ ምንም የሰው ኃይል ማከናወን ትችላለች:: ለሠራተኞች ስጋት ልትሆን ብትችልም፣ ለእዚህም መፍትሔ ይዛ መጥታለች:: ፕሮጀክቱ ለእነዚህ ሰዎች ስልጠና በመስጠት ሁለት ዓይነት የሥራ ዘርፎች አዘጋጅቶላቸዋል:: አንደኛው ሮቦቲክ ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የሚወገዱ ቆሻሻዎችን እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ነው::

ተማሪ ሀናንኤል ማስረሻ እና ጓደኞቿ ከቢሾፍቱ ፎቃ ስቲም ማዕከል በውድድሩ ላይ የተሳተፉ ናቸው:: በውድድሩም አግሪ ቴክ ሮቦት የተሰኘ የአፈር ጤንነት የሚመረምር የሮቦት ቴክኖሎጂ ይዘው ቀርበዋል:: ተማሪ ሀናንኤል እንደምትለው፤ በማዕከሉ ለሦስት ወራት ስልጠና ወስደዋል:: እነሱን ይህን ለመሥራት ያነሳሳቸው በአካባቢያቸው ያለውን ችግር በመመልከት በተለይ ግብርና ዘርፍ ላይ አተኩረው ለመሥራት በመፈለጋቸው ነው:: ለእጽዋት የተለያዩ የኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ ማዳበሪያዎችን ከመጠቀም ይልቅ አፈርን በመንከባከብ ተፈጥሯዊ የሆኑ እንደ ፍግ የመሳሳሉ ነገሮችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነት ለመጨመር በማሰብ ነው::

ሮቦቷ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላት ሲሆን፣ የአፈር ጤንነት በመለካት ማረጋገጥ ትችላለች:: አፈሩ ጤናማ ሆኖ ከተገኘ በነበረበት እንዲቀጥል ታደርጋለች:: አፈሩ ጤናማ ካልሆነ ግን በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገባቸው ተግባራትን በመዘርዘር ታመለክታለች:: የአፈሩን እርጥበት በመለካትም እርጥበቱ ከ50 በመቶ በታች ከሆነ መተግበሪያ ላይ እንዲታይ ታደርጋለች:: መተግበሪያው ሰው ሠራሽ አስተውሎት የተገጠመለት ስለሆነ ሊወሰድ የሚገባውን ርምጃ ወዲያውኑ በማሳወቅ ምላሽ እንዲሰጥ እንደምታደርግ ትገልጻለች::

ይቺ ሮቦት በፕሮቶታይፕ ደረጃ ስለተሰራች የምትሰራው በባትሪ ነው፤ በቀጣይ ሶላር ኢነርጂን መጠቀም እንድትችል ይደረጋል የምትለው ተማሪ ሀናንኤል፤ ሶላር ኢነርጂን በመጠቀም አካባቢን በመንከባከብ፣ የአየርና የአፈር ብክለት እንዳይኖር በማድረግ የሰው ልጆች ጤና እንዲጠብቅ ለማድረግ ታስችላለች ትላለች:: በቀጣይ የአፈር ጤንነት ከመጠበቅ ባለፈ የሙቀት መጠን መለካትና ውሃ ማጠጣት እንድትችልና በመስኖ ላይ እንድትሰራ ተደርጎ እንደምትሻሻል ትናገራለች።

በውድድሩ መጨረሻም ከተለያዩ ስቲም ማዕከላት የተወጣጡ 37 ፕሮጀክቶች መካከል በኮተቤ ስቲም ማዕከል አማካኝነት ለውድድር የቀረበው ‹‹አዳብቴብል ሮቦት›› አንደኛ በመውጣቱ በዓለም አቀፍ መድረኩ ኢትዮጵያን ወክሎ እንዲሳተፍ ተመርጧል::

ዓለም አቀፉ የሮቦቲክ ሮቦት ኦሎምፒያድ ውድድር እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2004 የተጀመረ መሆኑን መረጃዎች ጠቁመዋል:: የዘንድሮው /የ2024/ ውድድር እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር ከኅዳር 28 እስከ 30 በቱርክ ይካሄዳል። በውድድሩ ላይ ከ80 ሀገራት በላይ እንደሚሳተፉ መረጃዎች ያመላክታሉ::

# ወቅታዊ ትንታኔ

## ሕገ ወጥ ስደትን ለመከላከል የሚሰሩ ሥራዎች ምን ያህል ውጤታማ ናቸው ?

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

ሰሞኑን ሁለተኛው አህጉራዊ ዓለም አቀፍ የፍልሰት ስምምነት ጉባኤ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። ጉባኤው በተጀመረበት ወቅትም የፍትህ ሚኒስቴሩ ዶክተር ጌድዮን ጢሞቲዮስ ኢትዮጵያ የፍልሰተኞችን ጉዳይ በልማት ፖሊሲዎቿና እቅዶቿ ውስጥ አካታ እየሰራች መሆኑን ገልጸዋል። ሚኒስቴሩ በጉባኤው ላይ ባደረጉት ንግግርም ኢትዮጵያ እ.አ.አ በ2018 የጸደቀውን ዓለም አቀፍ የፍልሰት ስምምነትን በመተግበር ላይ ትገኛለች። በስምምነቱም ከተካተቱ ሃያ አጀንዳዎች ውስጥ ኢትዮጵያ አስሩን በተለያዩ የልማት ፖሊሲዎቿና እቅዶቿ ውስጥ ተካታው እንዲፈጸሙ በመሥራት ላይ ናት።

በዚህም መደበኛ ያልሆነውን ፍልሰት ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም መደበኛ የሆነውን ፍልሰት በማስፋፋት ከሕጋዊ ፍልሰት የሚገኘውን ጥቅም በማሳደግ በኩል ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ጠቁመዋል። ‹‹ኢትዮጵያ የፍልሰት መነሻ፣ መተላለፊያ እና መዳረሻ ሀገር ናት።›› ያሉት ሚንስትሩ በዚህም መነሻነት መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ሀገር አቀፍ የትብብር ጥምረት ካውንስል በማቋቋም እየሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

እኛም እነዚህ በመንግሥት በኩል እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች ከችግሩ አሳሳቢነትና ስፋት አንጻር ምን ያህል ውጤታማ ናቸው ሰንል ባለሙያዎችን አነጋግረናል።

በቀዳሚነት ምላሻቸውን እንዲያጋሩን ያነጋገርናቸው አቶ ደረጀ ተግይበሉን ነው። አቶ ደረጀ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚንስቴር የሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። አቶ ደረጀ እንደሚያብራሩት ወደ ውጭ ሀገራት በመሄድ ሥራ መሥራት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገራት ዜጎችም የሚፈጸምና ጠቃሚም ነገር ነው። በአሁኑ ወቅት በርካታ ሀገራት ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በሚላክ ገንዘብ ከውጪ ምንዛሬ ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ሲሆኑ ይታያል። ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ዜጎች በመደበኛ መንገድ መንቀሳቀስ ሲችሉ ብቻ ነው። መደበኛ ስደተኞች የሚባሉት በሕጋዊ መንገድ መንግሥት አውቋቸው በታወቁና ለዚህ ተብለው በተዘጋጁ ቦታዎች ስልጠና ወስደው ወደ ሌሎች ሀገራት ለሥራ የሚሄዱትን ነው። ኢትዮጵያም ይህንን አገልግሎት እንደ ሀገር ለዜጎቿ በነፃ ተደራሽ በማድረግ ላይ ትገኛለች።

በአሁኑ ወቅት መንግሥት በሕጋዊ መንገድ ለሚጓዙት ከተለያዩ ሀገራት ጋር ደመወዛቸውን፣ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችና መብታቸውን በተመለከተ ስለሚዋዋሉት ውል ጭምር ድርድር ማድረግ ጀምሯል። ይህ አሰራር እጅግ እየተሻሻለ መጥቶ በዲጂታላይዝድ መንገድ ምዝገባ መካሄድ ጀምሯል። ይህ በየመንደሩ በተደጋጋሚ በደላሎች ይጠየቁ የነበረውን ከፍተኛ ክፍያ የሚያስቀርም ሲሆን ዜጎቹም የትም ሀገር ቢሆኑ በመንግሥት በኩል መብታቸውን ለማስጠበቅ የሚሰሩ ሥራዎችንም ቀላል የሚያደርግ ይሆናል።

በሕጋዊ መንገድ መሄድ በጉዞ ወቅት ከሚደርስ እንግልትና ስቃይ ከመዳን ባለፈ መብትና ጥቅሞቻቸው ቀድመው የታወቁ በመሆናቸው ተረጋግተው እንዲቆዩ ይረዳል። ቀጣሪዎቻቸው ይታወቃሉ። በመሆኑም ጉዳት ከደረሰ፣ ገንዘባቸው ከተከለከሉ፣ የጉልበት ብዝበዛ ከተካሄደባቸው በቀላሉ መጠየቅ ይቻላል። ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት መንግሥት ጉዳዩን በቅርበት ስለሚከታተለው ችግሩን ለመቅረፍ በቀላሉ ይቻላል።


ለምሳሌ ኤጀንሲዎች ሠራተኞቹ የሰሩበትን ቢከለከሉ እዚህ ሆነው የሚከፍሉት ገንዘብ እንደ ዋስትና ያስይዛሉ። ‹‹ነገር ግን በሕጋዊ መንገድ በተጓዙት በኩል እስካሁን የከፉ ችግሮች አልተከሰቱም›› ያሉት አቶ ደረጀ ይህም ሆኖ ለኤምባሲ ያሳወቁና ችግሩ የተፈታላቸው መኖራቸውን አስታውቀዋል።

‹‹በቀጣይ አሰራሮችን ለማስተካከል የሚሰሩ ሥራዎችም ይኖራሉ።›› ያሉት አቶ ደረጀ ከዚህም ውስጥ አዲስ በወጣው ሕግ ላይ «ሌበር አታሼ» በየሀገራቱ እንደሚቀመጥ የተወሰነ በመሆኑ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል። እነዚህም ለሀገሪቷ ወኪል ሆነው የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነቱን የሚከታተሉ በየኤምባሲዎች የሚመደቡ ይሆናል።

እነዚህ ባለሙያዎች የሠራተኞች መብት ከተጣሰ ስምምነቱን መሰረት በማድረግ ለማስከበር ይሰራሉ። ይህም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ መንግሥት ለችግር የተዳረጉ ዜጎች መኖራቸውን ካወቀ ሊሰራ የሚችለው ከሀገራቱ ጋር በዲፕሎማሲያዊ መንገድ በመደራደር ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ማድረግ ነው። ይህ ግን ሁሌም ሊሳካ ስለማይችል በአሁኑ ወቅት በርካቶች በተለያዩ ሀገራት በስቃይ ውስጥ ይገኛሉ። ለዚህም በመንግሥት በኩል ችግሩን በመቅረፍ የዜጎችን መብትና ጥቅም ያስከብራሉ የሚላቸውን ሥራዎች በሙሉ ሲሰራ ቆይቷል በቀጣይም አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ይላሉ አቶ ደረጀ።



አቶ ደረጀ ተግይበሉ



አቶ አብርሃም አያሌው

በተጨማሪ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በተያየዘ ያለውን ግንኙነት ውጤታማ ለማድረግ የድንበር አስተደዳርን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያቶች የተደረጉና ወደፊትም የሚደረጉ ውይይቶች አሉ። ይህም ድንበሩን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል ? የጸጥታ ኃይሉን፣ መከላከያ፣ ኢምግሬሽን ሌሎች በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል ምክክር ይደረጋል። የዜጎችን መብት ከማስከበርና ጥቅሞቻቸውንም በማስጠበቅ ረገድ እንዲሁም የሕፃናትና ሴቶች ልዩ ፍላጎት ከማሟላት አኳያም የሚሰሩ ሥራዎች አሉ። የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በተለየ መልኩ ከፍተኛ ፍልሰት የሚታይበት በመሆኑ ለፍልሰተኞች ጉዳይ ምላሽ የሚሰጥ የአምስት ዓመት እቅድ በመያዝ እየተሰራ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት አብዛኛውን አሰራር ዲጂታላይዝድ እየተደረገ ነው። ይህ ደግሞ ደላሎችና ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠርና በወቅቱ ርምጃ ለመውሰድ በእጅጉ ጠቃሚ ነው። ይህም በሕገ ወጥ መንገድ የሚከናወኑ ተግባራትን በመግታት የዜጎችን መብትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ይሆናል። በተጨማሪም አሰራሮችን በዘመናዊ መንገድ በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ ማከናወን ያስፈለገው በአስፈጻሚው አካል በኩል ያለ የአገልግሎት አሰጣጡንም ሆነ ኤጀንሲዎችን ለመቆጣጠር ሁኔታዎችን የሚያመቻች በመሆኑ ነው።

ይህም ሆኖ ዛሬም ድረስ በሞባይል ስልክ መልእክት በመላክና በሌሎች መንገዶችም በሕጋዊ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት አገልግሎት ለማግኘት ምንም ክፍያ እንደሌለ ቢገለጽም ከመረጃ እጥረትና በቅርብ ላለ ሰው እምነት በመኖር ብዙዎች በሕገ ወጥ መንገድ በመጓዝ ለችግር እየተጋለጡ ይገኛል።

በሌላ በኩል ችግር ከመደረሱ በፊት ለመከላከልም እንደ መንግሥት የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራው በተለያዩ አካላት በስፋት እየተሰራበት ነው ያሉት አቶ ደረጀ በተለይም የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይን የሚመለከቱ ቢሮዎች ተቀዳሚ ሥራቸው አድርገው እያከናወኑት ይገኛል። በአንዳንድ ክልሎች ደግሞ አደረጃጀታቸው የሥራና ክህሎትን የሚመለከት ሲሆን የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተከፍቶ በመሥራት ላይ ነው። በእነዚህ ቢሮዎችም መረጃዎችን ተደራሽ የማድረግና ስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ እንቅስቃሴዎች ወረዳ ደረስ በመካሄድ ላይ ናቸው። በተጨማሪ ከመንግሥት ተቋማትና የሰው ኃይል ባለፈ በሴቶች ጉዳይ ላይ የሚሰሩ አደረጃጀቶችንም በመጠቀም እየተሰራ በመሆኑ በየወቅቱ አበረታች ለውጦች እየተመዘገቡ ይገኛል ብለዋል።

ሌላው ሃሳባቸውን ያካፈሉን በፍትህ ሚኒስቴር ብሔራዊ የፍልሰት ትብብር ጥምረት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ አብርሃም አያሌው ናቸው። እንደ አጠቃላይ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል ለማለት የሚያስደፍሩ ሥራዎች ተከናውነዋል ይላሉ አቶ አብርሃም ባለፉት ዓመታትም እንደ ሀገር ሲከናወኑ የቆዩ ሥራዎችን እንደሚከተለው ገልጸዋቸዋል። ለምሳሌ ባለፈው ዓመት በሕጋዊ መንገድ የተላኩት ሶስት መቶ አርባ አምስት ሺህ ዜጎች አደረጃጀት ተፈጥሮ ሕጎች ወጥተው በተቋማት ደረጃ ቅንጅት በመሰራቱ የተገኘ ውጤት ነው። እነዚህን ዜጎች በሕጋዊ መንገድ መላክ ባይቻል ኖሮ ኢመደበኛውን መንገድ በመጠቀም ለተለያዩ ችግሮች መጋለጣቸው የማይቀር ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘ የውጪ ምንዛሬ ገቢም «ረሚታንስ» በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር ማድረግ ተችሏል። በዚህም ዘንድሮ ብቻ ከአራት ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት ተችሏል።

ወንጀል በመከላከልም ረገድ በጣም አበረታችና ውጤታማ ሥራዎች ተከናውነዋል ማለት ይቻላል። እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊያዝ የሚገባው በኢመደበኛ የሰዎች ዝውውር ውስጥ የሚሳተፉ አካላት የሚሰሯቸው ወንጀሎች እጅግ የተወሳሰቡና ረዥም ሰንሰለት ያላቸው መሆናቸው ነው። የወንጀለኞቹ ግንኙነት ኢትዮጵያ ውስጥ በርቀት ከምትገኝ አንዲት የገጠር ቀበሌ ወይንም መንደር እስከ ደቡብ አፍሪካ እና ሌሎችም መዳረሻዎች የተዘረጋ ነው። መስኩ እንደ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይም ከጦር መሳሪያና ከአደንዛዥ እጽ ቀጥሎ ከፍተኛ የገንዘብ ዝውውር ያለበትም ነው። አጠቃላይ በሰዎች መነገድ በዓመት ከአንድ መቶ ሃምሳ ቢሊየን ዶላር በላይ የሚንቀሳቀስበት ነው። ይህን ጠንካራ እና ብዙ ቦታዎችን የሚያካትት ሰንሰለት ለመበጣጠስ የተጠናከረና የተቀናጀ ኃይልም ሥራም የሚያስፈልግ ይሆናል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በተሰሩ ሥራዎች በተወሰነ ደረጃ ለውጥ ማስመዝገብ ተችሏል።

በዚህ ረገድ ከተሰሩ ሥራዎች መካከል የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ይህንን ወንጀል ለመከላከል ብቻ ራሱን የቻለ ክፍል አቋቁሟል። በተመሳሳይ ዓቃቤ ሕግም ይህንን ወንጀል ለመመርመር፣ ለመከታተልና ወንጀለኞችን በሕግ ፊት ተጠያቂ ለማድረግ ራሱን የቻለ አደረጃጀት መስርቷል። በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ለዚህ አገልግሎት የሚውል ራሱን የቻለ ችሎት ተቋቁሟል። በዚህም እስከ ናይሮቢና ታንዛንያ ድረስ መስመራቸውን የዘረጉ ከደቡብ የሀገሪቱ ክፍል በሰዎች የሚነግዱ፣ ሰዎችን የሚበዘብዙና ኩላሊት እያወጡ የሚሸጡ ትልልቅ ወንጀለኞች ባለፈው ዓመት በቁጥጥር ስር ውለው ቅጣት ተላልፎባቸዋል። ይህም ሆኖ ወንጀለኞቹ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ በመሆኑ ከሌሎች ሀገራት ጋር በጥምረት መሥራትም የግድ የሚል ይሆናል።

በዚህም ረገድ ባለፈው ዓመት ከጅቡቲ ጋር የጋራ የወንጀል ምርመራ ቡድን ለማቋቋም የመግባቢያ ሰነድ ለመፈራረም ተችሏል። በዚህም በኢትዮጵያ በኩል ከየክልሉ ጀምሮ ያሉ ወንጀለኞችን ድሬዳዋና ጋላፊ ደረስ የመለየት ሥራ የሚሰራ ይሆናል። በጅቡቲ በኩልም በእነሱ በኩል ያሉትን በመለየት የጋራ የምርመራ ቡድን ተቋቁሞ የመረጃና የማስረጃ ልውውጥ በጋራ እየተደረገ ነው። ከኬንያ ጋርም ሁለት ጊዜ ንግግሮች ተደርገዋል። በዚህም ረገድ ዋናውን ወንጀል የሚሰሩ የሚመለምሉ፣ የሚቀበሉና የሚያሻግሩ ከሞያሌ ጀምሮ እስከ ናይሮቢ ድረስ ያሉት መሆናቸው ይታወቃል። ይህንንም ለመፍታት ከኬንያ የሕግ አስከባሪ አካላት ጋር አዲስ አበባ ድረስ መጥተው ውይይት ተጀምሯል።

በሌላ በኩል እኤአ በ2022 ሃያ ዘጠኝ ኢትዮጵያውያን በማላዊ ጫካ ውስጥ ተገለው ተገኝተው ነበር። እነሱን በተመለከተ የሀገሪቱ መንግሥት ወንጀል የፈጸሙትን ሰዎች ለሕግ ለማቅረብ እየሰራ ይገኛል። ነገር ግን አሁንም ድረስ በርካታ ዜጎች በእስር ቤት ውስጥ የሚገኙ አሉ። ለዚህም ከማላዊ ጋር የሁለትዮሽ ንግግር ለማድረግ የተጀመሩ ሥራዎች አሉ። ይህ አጋጣሚ በማላዊ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሀገራት እየተከሰተ ያለ በመሆኑ ዜጎች ባሉባቸው የመተላለፊያና የመዳረሻ ሀገራት ጋር የሚደረገው ውይይት የሚቀጥል ይሆናል።

በቅርቡም ከጅቡቲ ጀምሮ እስከ ሳውድ አረቢያ ያሉ ሀገራትን የሚያካትት በሚንስትሮች ደረጃ የሚደረግ ውይይት ይኖራል። የዚህ ዓላማም ዜጎች ከሀገራችን ወጥተው የሚሄዱት ሌላ ሀገር ለመውረር ወይንም ስጋት ለመሆን አይደለም። አሁን ላሉበት ነገርም የሚዳረጉት በሕገ ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ነው።

ይህንን በተመለከተ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገራት የፈረሙት ስምምነት አለ። ስምምነቱ ሀገራት ወደነሱ የገቡ ፍልሰተኞችን እንደ ወንጀለኛ ሳይሆን እንደ ተጎጂ አይተው ጥበቃ እንዲያደርጉላቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ ባለፈም እዛ ባሉበት ወቅትም እንደ እስር ሳይሆን በተለየ ማቆያ አቆይተው ከሀገራቸው መንግሥት ጋር በመነጋጋር እንዲመልሷቸው የሚል ነው። በተጨማሪ እንደ ፍትህ ሚኒስቴር ወንጀለኞችን አሳልፎ የመስጠት በሕግ ጉዳዮች በትብብር ለመሥራት ከኬንያና ከደቡብ አፍሪካ ጋር ስምምነት ተጀምሯል። እነዚህ ሁሉ ተግባራት በአጭር ጊዜ የተሰሩ መሆናቸው እንደ ሀገር በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ትኩረትና አመርቂ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን አመላካች ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ከስደት መልስ ባለነገዋ የሴቶች ማገገሚያ ማዕከል

**አመለወርቅ ከበደ**

> **ብዙ ቦታዎች ላይ ሴቶች አቅም የላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ ተቀባይነት የላቸውም:: ይሄ ቤት ሴቶች አቅም እንዳላቸው እና ያን አቅማቸውን አውጥተው ለማሳየት ትንሽ ድጋፍ ብቻ እንደሚፈልጉ ነው የሚያሳየው**



ፎቶ፡- ገበየ ገብሬ

**ሲሳይ ግዛው**

ሲሳይ ግዛው ገና የቤተሰብ ድጋፍ በሚያስፈልጋት እድሜ ላይ እያለች ነበር ወላጅ አባቷ በድንገት በሞት የተለዩት:: ልጆቹን የማሳደግ ኃላፊነት የሲሳይ ወላጅ እናት ላይ ያረፈ ቢሆንም እናት ከዚህ በፊት የባል እጅ ብቻ አይተው የሚኖሩ ስለሆነ ከቤት ወጥተው ሥራ ፈልጎ ለመሥራት እውቀት አልነበራቸውም::

በዚህ ምክንያት ሲሳይ ቤተሰቡን ለመደገፍ ትምህርቷን አቋርጣ የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ጀመረች:: የተለያዩ ሥራዎች በምትሰራበት ወቅት ባፈራቻቸው ጓደኞች ተፅዕኖ ወደ ሱስ ሕይወት ለመግባት ተገደደች:: የሱስ ሕይወቷ እሷን ከመጉዳት አልፎ ቤተሰቦቿን እያስመረረ ስለመጣ እና ከነበረችበት የኑሮ ሁኔታ የተሻለ ነገር ባገኝ በማለት በሕገ ወጥ መንገድ መሰደድን መረጠች::

ተሰዳ በሄደችበት ሀገርም በሴቶች ያልተለመዱ ሥራዎች ሰርታለች:: ሆኖም በስደት ለ፲ ዓመታት ብትቆይም እንዳሰበችው ሊሳካላት አልቻለም:: የስደት ኑሮ አልሳካ ሲላት ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰች:: እዚህም ቢሆን የኑሮ ፈተና ቀጠለ:: ሥራ አጥነቱ ከኑሮ ክብደቱ ጋር ተዳምሮ ለሲሳይ ሕይወት የስቃይ ሆነ:: ኑሮም ከዕለት ወደ ዕለት ፈታኝ ሆነባት::

ሲሳይ ትውልድና እድገቷ አዲስ አበባ ከተማ ነው:: ለቤተሰቦቿ አምስተኛ ልጅ የሆነችው ሲሳይ፤ ትዳር መስርታም ሶስት ልጆችን አፍርታለች:: እነዚህ ሁሉ ቤተሰብ አባላት ደግሞ ሲሳይን እጅ የሚጠብቁ ናቸው::

ቤተሰቦቿን ለመደገፍ ቆሎ፣ ድንች እየሸጠች ሲሆን፤ የተለያዩ የቀን ሥራዎችንም ከመሞከር አልቦዘነችም:: "እናታችንን ለመደገፍ እኔም ሆንኩ እህቶቼ ብዙ ነገር አድርገናል:: ምክንያቱም እናታችን ተሯሩጣ ቤተሰቡን ማስተዳደር አትችልም:: አባታችን የሞተው ደግሞ በአጋጣሚ ስለሆነ ቤትን መምራት ዝግጁነት አልነበረንም " ስትል ትናገራለች::

ሲሳይ የተሻለ ሕይወት አግኝታ እራሷን እና ቤተሰቦቿን ለመርዳት ወደ ቤሩት ብትሄድም እንዳሰበችው ከስኬት ልትደርስ አልቻለችም:: "አረብ ሀገር ለመጀመሪያ ጊዜ ስሄድ የደረሰኝ የእርሻ ሥራ ነው:: በሀገሬ ላይ ያላረስኩትን እርሻ አረብ ሀገር ላይ አርሻለሁ::" ስትል ትናገራለች::

"የተወለድኩት ከተማ እንደመሆኑ እና ሴት እንደመሆኔ የእርሻ ሥራ የመሥራት ልምዱም ሃሳቡም አልነበረኝም:: ነገር ግን እዚህ በነበርኩበት ጊዜ በውድቅት ሌሊት እየሰከርኩ ወደ ቤት እየመጣሁ እናቴን በጣም አስቸግራት ነበር፤ በዚህ የተነሳ እናቴ በጣም ተናዳ እስኪ እንደ ሰው አረብ ሀገር እንኳን ሄደሽ ሙቺ ነው ያለችኝ::" በማለት ወደ አረብ ሀገር የሄደችበትን ምክንያት ታስታውሳለች::

ሲሳይ ወደ ቤሩት ልትሄድ የቻለችበትን አጋጣሚ ስትናገር፤ "ከመሄዴ በፊት ሥራ ስሰራ የነበረው በ70 ብር ነበር:: ያን ብር በሳምንት እያመጣሁ ለእናቴ ብሰጣትም ቤተሰቡን ለማስተዳደር በቂ አልነበረም:: በዛ ላይ ጓደኞች ስይዝ ሱስ ውስጥ ገባሁ:: እናም ገንዘቡ እንኳን ለቤተሰቡ ለእኔ እንኳን የማይበቃ ነው::" ስትል ትናገራለች::

እሷ ወደ ቤይሩት ከመሄዷ በፊት ቀድሞ ቤይሩት የሚኖሩ ጓደኞች ነበሯት:: የምትሰራውን እና የምታገኘውን ገንዘብ ስትነግራቸው፤ "እንዴት እንደዚህ ዓይነት ሥራ በዚህ ገንዘብ ትሰሪያለሽ" በማለት እነሱ በሚኖሩበት ቦታ የተሻለ ገንዘብ እንደሚከፈል ነግረዋት ወደነሱ እንድትመጣ አግባቧት፤ ባለታሪኳም ምክራቸውን ሰምታ ለስደት ተነሳች::

"ጓደኞቼ ፓስፖርት ለማውጣት ብቻ ነበር ገንዘብ የላኩልኝ:: ሆኖም ጓደኞቼ እንደነገሩኝ ሳይሆን የገጠመኝ ሥራ ሴት ልጅ የማትሰራው እጅግ አድካሚ ሥራ ነበር:: ከሄድኩ በኋላ የእርሻ ሥራ ገጠመኝ የምትለው ባለታሪኳ፤ አንዲት ሴት አረብ ሀገር ሄደች ማለት ስኬታማ ሆነች ማለት አይደለም:: መራብና ሌሎች ችግሮችም እኮ አሉ::" ስትል ታስረዳለች::

"አላርስም ብዬ ብመጣ እናቴ ሊሰማት የሚችለውን ስሜት አሰብኩ፤ በአካባቢውም ሊወራ የሚችለውን ወሬ ገመትኩ፤ ተመልሼ ብመጣ ያመጣት ሱሷ ነው እንደሚሉኝም ተረዳሁ:: ዓላማ መጀመሪያም የላትም ተብሎ እንደሚወራብኝ ስላሰብኩ አንገቴን ደፍቼ የእርሻ ሥራዬን ቀጠልኩ::" ትላለች::

ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያለው ቤተሰብ ሲኖር፤ ያለውን ችግር ለመሙላት ቀጣይ የሕይወት ዓላማን ለማሳካት ገንዘብ መቆጠብ አስቸጋሪ ነገር ነው የሚሆነው:: ሲሳይ ቤይሩት በምትኖርበት ወቅት ሰርታ የምታገኘውን ገንዘብ ከስር ከስር ለቤተሰቦቿ ስለምትልክ የራሷን ሕይወት ለማሻሻል ገንዘብ የመቆጠብ እድል አላገኘችም:: ወደ ሀገሯም ስትመለስ ባዶ እጇን ነበር::

አሁን ላይ ከአረብ ሀገር ከተመለሰች አራት ዓመት ሆኗታል:: በእነዚህ ዓመታት የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት ብታደርግም ውጤታማ ልትሆን አልቻለችም:: "ከአረብ ሀገር ከመጣሁ በኋላ የጀበና ቡና ንግድ ጨምሮ የተለያዩ ንግዶችን ብጀምርም ሊሳካልኝ አልቻለም:: ምክንያቱም ቸገረኝ ላለ ሁሉ መስጠት በጣም አበዛ ነበርና ገንዘብ መያዝ አልቻልኩም::" ስትል ትናገራለች::

ወደ ለነገዋ የሴቶች ማገገሚያ ልትገባ የቻለችበትን አጋጣሚ የምትናገረው ሲሳይ፤ "መሥራት እየቻሉ እድል አጥተው እቤት የተቀመጡ ሴቶች ከየክፍለ ከተማው ተመርጠው ወደ ሴቶች ማዕከል እንዲወጡ መረጃ ተልኮ ነበር:: ከአረብ ሀገር ከመጣሁ በኋላ ሶስት ልጆቼን ጥዬ ነው የተለያዩ ሥራዎችን ስሰራ የነበረው:: በሥራዬ ውጤታማ ስላልሆንኩ ሌላ አማራጭ እፈልግ ነበር:: ለነገዋ ማዕከል የመግባት እድሉን ሳገኝ ልሞክር ብዬ ነበር የገባሁት::" ስትል ትገልጻለች::

ባለታሪኳ ለረጅም ዓመታት የተለያዩ ሥራዎችን ብትሰራም ያገኘችው ምንም ውጤት አለመኖሩን የሚመለከቱ የአካባቢው ሰዎች በጣም ነበር የሚያዝኑላት:: በዛ ላይ ከእናቷ ቤት ወጥታ ብቻዋን ተከራይታ እንደምትኖር ስለሚያውቁ ወደ ማዕከሉ ገብታ እራሷን መለወጥ እንደምትችል በማመናቸው ወደ ነገዋ ሴቶች ማዕከል እንድትገባ ገፋፏት:: ምልመላው የሚደረገው በቀበሌ በኩል መሆኑን ስትሰማ ከዚህ በፊት ለቀበሌ አካላት አሉታዊ አመለካከት የተነሳ ላለመሄድ አቅማምታ ነበር::

ሲሳይ እንደምትለው "ጎረቤቶቼ የለፋሁትን እና ያገኘሁትን ጥቅም ሲመለከቱ "ማረፍ በሚገባሽ ጊዜ መባከንሽ ያሳዝናል" እያሉ ያዝኑ ነበር:: አንድ ቀን ከሥራ መጥቼ ምግብ እየበላሁ እያለ፤ እንደዚህ ዓይነት ማዕከል አለ:: ቀበሌዎች እየመለመሉ ስለሆነ ሂጂ አሉኝ:: የቀበሌ ነገር ከሆነ አልፈልግም ስላቸው፤ ግዴለሽም የምትለወጪበት ነው ብለው ለመኑኝ:: ስንት ወር እንደሚፈጅ ስጠይቃቸው ሶስት ወይም ስድስት ወር ሊፈጅ እንደሚችል ሲነግሩኝ ልሞክር ብዬ መጣሁ::" ትላለች::

መጀመሪያ ወደ ማዕከሉ ስትመጣ ገና ከግቢ ጀምሮ የተመለከተችው ነገር ልቧን እንደሳበው የምትናገረው ሲሳይ "እንዴ ዱባይ እዚህም አለ እንዴ ! ነው ያልኩት" ስትል መደነቋን ትገልጻለች:: ወደ ማዕከሉ ከገባች በኋላ የተመቻቸላቸው እድል ስለመመለስ እንዳታስብ እንዳደረጋትም ታስረዳለች::

"ውጭ ላይ ስኖር ብዙ የሚያሳስቡኝ የኑሮ ጥያቄዎች አሉኝ:: የምበላው ምግብ፣ ሥራዬ፣ የቤት ኪራይ ጨምሮ በርካታ ነገሮች ያስጨንቁኛል፤ ማዕከሉ ውስጥ ግን እነዚህን ጭንቀቶቼን ጥዬ ነው ትምህርቴን እየተከታተልኩ የነበረው:: ምክንያቱም የምማረው ምግብ፣ ውሃ እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ቀርበውልኝ ነው::" ትላለች::

"አረብ ሀገር ተብሎ የሚወራለት ስሙ ብቻ ነው:: ምናልባት ገንዘቡ ሲገኝ ሊያስደስት ይችላል:: ነገር ግን የሚከፈለው ዋጋ በጣም ከፍተኛ ነው:: እኔ አረብ ሀገር በጣም ብዙ ዋጋ ከፍያለሁ:: ከዛ ወደ ነገዋ የሴቶች ተሃድሶ ማዕከል ገብቼ ያገኘሁት ጥቅም እጅግ የላቀ ነው::" ስትል ትገልጻለች::

በማዕከሉ ስድስት ወር ቆይታዋ የልብስ ስፌት ስልጠና ወስዳ ተመርቃለች:: ሲሳይ እንደምትለው፤ ቀደም ብሎ በአካባቢዋ ጨርቃ ጨርቅ ድርጅት ላይ የሚሰሩ ሰዎች ስትመለከት ለሥራው ፍላጎት ስላደረባት በጨርቃ ጨርቅ ድርጅት ሄዳ ተቀጠረች:: በድርጅቱ ብትቀጠርም መሥራት የቻለችው ልብስ መተኮስ ብቻ ነው::

"ከዚህ በፊት እኛ አካባቢ ጨርቃ ጨርቅ ላይ ስለሚሰሩ ሰዎች ወሬ ስሰማ፤ ልብስ ስፌት የመልመድ ፍላጎት ስለነበረኝ፤ ሥራ ተቀጥሬ በአንድ ሰዓት 60 ሸሚዞች እተኩስ ነበር፤ ነገር ግን ወደ ስፌት ለመሄድ እድሉን አላገኘሁም:: ምክንያቱም መጀመሪያ የሆነ ቦታ ሰርተሽ ከዛን በሂደት ነው ወደ ልብስ ስፌት የሚደረሰው፤ እኔ ግን ካለኝ ፍላጎት በመነጨ ትዕግስቱ አልነበረኝም::" ትላለች::

"እዛ ስሰራ ልብስ መስፋት እፈልግ ነበር የምትለው ባለታሪኳ አሁን ጊዜው ደርሶ እግዚአብሔር ፈቅዶ የራሴ ማሽን ተበርክቶልኝ ልብስ የምሰፋ ሴት ነኝ:: አሁን ያገኘሁትን ነገር ከድሮ ሕይወቴ ጋር ሳነጻጽር፤ በጣም ከመደሰቴ የተነሳ ቃላቶች ያጥሩኛል:: እዚህ ደረጃ እደርሳለሁ ብዬ አስቤም አላውቅም:: እናም እራሴን እንደ እድለኛ ነው የምቆጥረው::" ስትል ትናገራለች::

ቀደም ሲል ሲሳይ በጣም ተደባዳቢ ከመሆኗ የተነሳ በሆነ ወቅት ለእስር ተዳርጋለች:: ከዚህም በተጨማሪ ካራንቡላ የሚባል የቁማር ዓይነት ሱስ ሆኖባት ነበር:: ማዕከሉ ገብታ ያገኘችው የሕይወት ክህሎት ስልጠና እነዚህን እኩይ ተግባራት እንድትተው ረድቷታል::

መለወጥ የሚችሉ ሴቶች እጅግ በጣም መለወጥ የሚችሉበት ቤት ቢኖር የነገዋ የሴቶች ማዕከል ነው:: ምክንያቱም ምንም ዓይነት የሚያደናቅፋቸው ነገር የለም:: ውጭ ላይ ያለው ሕይወት ለተለያዩ አላስፈላጊ ነገሮች ያጋልጣሉ፤ በተለይም ሕይወት ከባድ ነው:: እንኳን እንደኛ ዓይነት ምንም ዓይነት ነገር የሌላቸው ሴቶች ቀርተው፤ ጥሩ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሰዎች እንኳ የተለያዩ የኑሮ ጥያቄዎች ያስጨንቃቸዋል::

ብዙ ቦታዎች ላይ ሴቶች አቅም የላቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ ተቀባይነት የላቸውም:: ይሄ ቤት ሴቶች አቅም እንዳላቸው እና ያን አቅማቸውን አውጥተው ለማሳየት ትንሽ ድጋፍ ብቻ እንደሚፈልጉ ነው የሚያሳየው::" በማለት፤ በየጎዳናው ያሉ፣ ከስደት ተመላሽ የሆኑ፣ አማራጭ አጥተው እቤት የተቀመጡ እና በተለያዩ ቦታዎች አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሴቶች እድሉን አግኝተው ቢመጡ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ታስረዳለች::

በትምህርትም ሆነ በሙያ ደረጃ እውቀት ከፍ እያለ ይሄዳል እንጂ አያንስም የምትለው ሲሳይ፤ በቀጣይ አሁን ያለችበትን የሙያ ደረጃ ለማሻሻል እና የራሷን ሥራ ጀምራ ሌሎች ሴቶችን እየረዳች ይዛ ለመቀጠል ፍላጎት እንዳላት ታስቀምጣለች::

በመጨረሻም "እኛን እንደ ሰው አስባ ይህን ማዕከል በማቋቋም የሙያ ባለቤት ስላደረገችኝ ከንቲባ አዳነች አቤቤን አመሰግናለሁ:: መምህራኖቻችን ባህሪያችንን ችለው ክትትላቸው ሳይለየን እዚህ ስላደረሱን እያመሰገንኩ፤ አስተዳደር ቢሮ ከላይ እስከታች ያሉ ሠራተኞች እና ክሊኒክ አካባቢ የሚሰሩትን ባለሙያዎችንም ላመሰግን እወዳለሁ::" በማለት ሃሳቧን አጠቃላለች::

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ግርማ መንግሥቴ

የዛሬው "አዲስ ዘመን ድሮ" በአንድ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ከመጽሐፍት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ "አዲስ ዘመን" ልክ እንደ ዛሬው ሁሉ፣ ድሮም ለንባብና ጽሕፈት፤ እንዲሁም ለድርሰትና ደራሲ፤ በአጠቃላይም ስለ መጽሐፍት፣ ስለ ሥነእውቀትና ፋይዳው ልዩ ትኩረትን ሰጥቶ እንደ ነበር እንመለከታለን። በተለይም የመጀመሪያው ጸሐፊ (ታኅሣሥ 27 ቀን 1952 ዓ.ም) ምን ያህል ያኔ ላይ ሆነው የእኛን ዛሬ እንደተመለከቱ ለተገነዘበ ልባም ጉዳዩ ተዓምር ቢያሰኝ የሚገርም ሊሆን አይችልም። መልካም ንባብ።

**"መጽሐፍ የተጻፈው እኛ ልንጠቀምበት ነው"**

ተመልካችነት ያለው ሰው ሁሉንም ማስተዋልና መመልከት እንደሚጠቅመው ይገነዘበዋል። ይልቁንም መጽሐፉ መመልከትን ከሁሉ ያበልጠዋል።

አንድ ታላቅ ደራሲ ጥሩ አስተያየት ያለበት መጽሐፍ አዘወትሮ የተመለከተ እንደ ሆነ ከኔ በላይ ሌላ አዋቂ የለም የሚል ሃሳቡን ያሻሽልበታል። ከሰው በላይ ሰው እንዳለ የሚታወቀው ከድርሰት ወይም ከመጽሐፍ በላይ የሆነውን የድርሰት መጽሐፍ በመመልከት ነው።

የዓይን ምሳ፣ የመንፈስ ምግብ፣ የልብ ስቴ ወይን፤ የጥሩ ድርሰት ምንጭ ከሆነ መጽሐፍ በቀር ሌላ ምን ይገኛል? ቅዱስ ጳውሎስ "የተፃፈው ሁሉ እኛ ልንመክርበትና ልንገሥፅበት ተፅፏል" እንዳለው መጽሐፍት ባይኖሩ ምክርና ተግሳፅ የሚሆኑ፤ ጥበብና እውቀትን የሚገልፁ፤ የሰው ልጆችን የሚያጨዋውቱ የተሻሉ ነገሮች ባልተገኙም ነበር።

አዲሶቹም የጥበብ መጽሐፍት፣ የድሮዎቹም የቅዱስ መጽሐፍና የታሪክ ዜናዎች የሰውን አዕምሮ ለመክፈት ሃሳብን በማትባት ምን ያህል እንዳገለገሉ የመጽሐፍት ወዳጆች ሁሉ አይዘነጉትም።

"ሰው በሕይወቱ ሳለ ደስ ከሚያሰኘውና ከሚያደርገው መልካም ነገር በቀር ሌላ መልካም ነገር እንደሌለ አወቅሁ" ሲል ቃሉ መጽሐፍ ሆኖ የቀረበለትና መጽሐፉ በስሙ ሲጠራለት የሚኖረው ብልሁ ሰለሞን የተናገረው፤ ከመልካም ነገር የበለጠ ሌላ የመልካም መልካም የሆነ ምን መልካም ነገር ኖሮ ነው? በፍቺው አንባቢዎች ይደርሱበታል።

ከዚህም ዝቅ ብሎ "እግዚአብሔር ያደረገው ሁሉ ለዘለአለም እንዲኖር አወቅሁ" ካለ በኋላ በዚሁም ላይ "ይጨመርበትም፣ ይጎድልበትም ዘንድ አይችልም" ሲል ይኸው ፈላስፋ ንጉሥ የተናገረው የሰውን ሃሳብ በምን ግምት ላይ ለመጣል አስቦ ነው?። የዚህም ፍጅታ ለአንባቢው ተለቆለታል።

ይልቁንም ይኸው ፈላስፋ ንጉሥ "እንጀራህን በውሃ ላይ ስደድ (ጣል)። ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህና" ያለው ከመቸውም ይልቅ ፍቺውን ያገኘው ዛሬ እንደ ሆነ መረጃው ተገኝቷል።

በአሁኑ ክፍለ ዘመን ወንዞችን እየገደቡና ወራጆችን እያገዱ፣ ባሕሮችን በአስተላላፊ መዘውር እየጠለፉ በመስኖ ተግባር የሀብት እንጀራን ማግኘትና የሙብራት ኃይሎችን ሙብራት መዘርጋት የሚመለከተው" እንጀራህን በውሃ ላይ ስደድ፣ ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህና" የተባለውን የድሮውን የሳይንስ ሊቅ አሳብ ነው።

የሚያስታርቃቸው እያጡ ነው እንጂ የሃይማኖትና የሳይንስ መጽሐፍት ምንም አይጣሉም። ዙረው ተመልሰው የሚያስረዱት የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ ለጥበበኞች ጥበብን ገላጭ ነው።

"ነፉስ የሚጠብቅ አይዘራም፤ ደመናም የሚመለከት አያጭድም" እንደሚባለው፣ የሳይንስን መጽሐፍ የሚጠራጠር፣ ወይም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተባብል ከሁለት ዛፍ የወደቀ ይሆንና ባንዱም ሳይጠቀም ይቀራል።

የመጨረሻው የሀሳብ ውሳኔ "ከማለዳ ጀምረህ ዘርህን ዝራ፣ በማታም ጊዜ እጅህን አትኮርኩም" የተባለውን በመገንዘብ አሳብን ከምርመራ፣ እጆችን ከሥራ መሰብሰብ እንኳን ለአሁኑ ጊዜና ለመቸውም ትውልድ ተገቢ አይደለም።

ከመጽሐፍ ወዳጆች አንዱ

**(አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 27 ቀን 1952 ዓ•ም)**

* * * *

በመጽሐፍ ያለው እየታሰበ ሲሄድ በመጽሐፍ የሌለ እየተዘነጋ በመሄዱ ምክንያት ለታሪክ አወራረስና ለቃላት ጥናት ያለ መጽሐፍት ምንም ሊደረግ አይቻልም።

"ዘጻሐፍኩ ጾሐፍኩ" እንደ ተባለው ያለፉት ሊቃውንቶች የጻፉትን ጽፈዋል። የዛሬዎቹም የሚጽፉትን ይጽፋሉ።

ነገር ግን በስመ ሰው በእውቀትና በሊቅነት ወይም በጀግንነትና በሌላም ስመ ጥሩነት ሁሉ እኩል እንዳይደለ በስመ መጽሐፍም ሁሉ እኩል አይደለም።

እንደ እውነቱ የሆነ እንደ ሆነ የመጽሐፍ መጽሐፍ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ያለጥርጥርና ያለውልውል መጽሐፍ ነው ሊባል ይችላል።

ሰው አዲስ እየመሰለው በአሁኑ ዘመን ሁናቴ ሲደነቅና ሲገረም ይታያል። ባነጋገር እየተለያየና ባመራመር እየተሳሳተ ነው እንጂ። ሳይንስ ለሚባለው ዘመናዊ የጥበብ ምንጭ መሠረቱ ይኸው መሆኑ የታወቀ ነው። ሌላውም ዘመናዊ ፖለቲካና የእርስ በእርስ አለመስማማት ቀደም ብሎ የተነገረው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

"ምናሴ ኤፍሬምን፣ ኤፍሬምም ምናሴን ይበላዋል" የተባለው ቃል የሰጠው ትርጉም ተሠርቶበት በቅቷልን? ወይስ ሲሠራበት ይኖራል?

መጽሐፉ ምናሴና ኤፍሬም በማለት የመላውን ዓለም ሕዝቦች በሁለት መድቦ በሁለት ስም እንደ ተናገራቸው ሲታሰብ ከመቼውም ይልቅ ይህ ሁናቴ በአሁኑ ጊዜ የዓለም መረጃ ሳይሆን እንደማይቀር ይታወቃል።

ይኸውም ምሥራቅና ምዕራብ የተባለው የሁለት ፖለቲካ ክበብ መሆኑ አይጠረጠርም። ጦርነትም ይደረጋል እየተባለ የሚጠረጠረውና እርስ በእርሳቸው ይበላላሉ እየተባሉ የሚታሙት ወገኖች ያሉበት ወዲህና ወዲያ የብረት መጋረጃ ክልል ነው።

"ቀንድህን ብረት፣ ጥፍርህን ነሐስ አደርግልሀና ብዙ አሕዛብን ትሰብራለህ" ተብሎ ሚኪያስ በተባለው ነቢይ እንደ ተነገረው፤ የአሁኑ ዘመን ሕዝቦች ቅድድማቸው መሣሪያዎቻቸውን ሁሉ ኃይለኞችና አጥፊዎች ለማድረግ ስለሆነ ከላይ የተነገረውና ከዚህ የተገለፁት ሁለቱ ትንቢቶች በአሁኑ ጊዜ የጉዳት አስከታይ ተግባር መፈፀሚያ እንዳይሆኑ በተለይ የፀሎት መጽሐፍቶች የእግዚአብሔርን የምሕረት ደጅ ይጠባበቃሉ።

**(አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 28 ቀን 1952 ዓ•ም)**

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ የጦር ምርኮኞችን ገድላለች መባሏን ዩክሬን አወገዘች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ የማረከቻቸውን ዘጠኝ የዩክሬን ወታደሮችን ገድላለች መባሏን የዩክሬን የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅት አወገዘ። ድርጅቱ የሩሲያ ኃይሎች በድንበር አካባቢ በሚገኘው ከርስክ ክልል የማረኳቸው የዩክሬን ወታደሮች ላይ ግድያ ፈጽሟል ብሏል።

የድርጅቱ ኃላፊ ዲሚትሮ ሉቢኔትስ ሩሲያ “ሁሉንም የጦርነት ሕጎች እና አሠራሮች” ጥሳለች ሲሉ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና ለቀይ መስቀል ቅሬታቸውን መጻፋቸውን ተናግረዋል።

ኃላፊውን ይህንን ያሉት የዩክሬን የጦርነት ውሎዎችን የሚተነትነው ድረገጽ፣ ዲፕስቴት የሰው አልባ አውሮፕላን ኦፕሬተሮች ናቸው ያላቸውን ወታደሮች አስክሬን በድሮን በተቀረጸ ቪዲዮ ማውጣቱን ተከትሎ ነው። የሩሲያ ባለሥልጣናት ስለቀረበባቸው ክስ እስካሁን አስተያየት አልሰጡም።

ዩክሬን ባልተጠበቀ ሁኔታ የሩሲያን ድንበር ዘልቃ በመግባት ከፈጸመችው ወረራ ጀምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቿን በድንበር አካባቢ እንዳሰማራች ይታመናል።

በዲፕስቴት ድረ ገጽ በታተሙ ምስሎች ላይ የውስጥ ሱሪ ብቻ ያደረጉት የዩክሬን ወታደሮች አስከሬኖች በሆዳቸው በኩል ተንጋለው ይታያሉ። አስከሬናቸው የታየበት ስፍራ የእርሻ ቦታ ነው የተባለ ሲሆን ቢቢሲ እነዚህን ምስሎች በተናጠል ማረጋገጥ አልቻለም። ድረገጹ የገለፀው እነዚህ የዩክሬን ወታደሮች በሩሲያ ኃይሎች መገደላቸውን ነው።

“እነዚህ ተግባራት ሳይቀጡ መታለፍ የለባቸውም። ጠላት ሙሉ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል። ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲህ አይነት ወንጀሎችን ችላ ሊል አይገባም” ሲሉ ዲሚትሮ በቴሌግራም ገጻቸው አስፍረዋል።

ዩክሬን በጄኔቫ ስምምነት መሠረት የጦር ወንጀል የሆነውን ምርኮኞችን በመግደል ሩሲያን በተደጋጋሚ ስትወነጅላት ይሰማል። ከጥቂት ሳምንታት በፊት የዩክሬን ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የሩሲያ ኃይል 93 የዩክሬን የጦር ምርኮኞችን ገድሏል የሚል ሪፖርት አቅርቦ ነበር።

በምሥራቃዊ ዶኔትስክ ክልል በተፈጸመው የ16 የጦር ምርኮኞች ግድያ ላይ ምርመራ መክፈቱን አክሎ ገልጿል። ሩሲያ ወታደሮቿ በዩክሬን ጦርነት የጦር ወንጀል ፈጽመዋል መባሏን አትቀበልም ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## በትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ አቅራቢያ ሽጉጥ ይዞ የተገኘው ግለሰብ ታሰረ



ዶናልድ ትራምፕ በካሊፎርኒያ የምርጫ ቅስቀሳ እያደረጉ ባሉበት መድረክ አቅራቢያ ሁለት ያልተመዘገቡ ሽጉጦችና ሐሰተኛ ፓስፖርት ይዞ ተገኝቷል የተባለው ግሰለብ በቁጥጥር ሥር መዋሉን ፖሊስ ገለጸ። የ49 ዓመቱ ተጠርጣሪ ቬም ሚለር ጥቁር መኪና እየነዳ ሳለ ነው በፖሊስ እንዲቆም ታዞ ፍተሻ የተደረገበት። ፖሊስ ከመኪናው ውስጥ ሁለት ሽጉጥ እና “ብዙ ጥይቶች ያሉት ካርታ” ማግኘቱን ይፋ አድርጓል።

በቁጥጥር ሥር የዋለው ግለሰብ ምርመራ እየተደረገበት እንደሆነ የአካባቢው ፖሊስ ኃላፊ አሳውቀዋል። የአሜሪካ የደኅንነት መሥሪያ ቤት ሲክሬት ሰርቪስ ግለሰቡ ለትራምፕ “አደጋ የሚሆን አይደለም” ብሎ ምንም ዓይነት ግርግር እንዳልተፈጠረ አስረድቷል።

የአካባቢው ፖሊስ በቁጥጥር ሥር የዋለውን ግለሰብ “ወፈፌ” ሲሉ የገለፁት ሲሆን የትራምፕ ምርጫ ቅስቀሳ ታዳሚዎች ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት አልደገነም ብለዋል። ነገር ግን አሁንም በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ አላገኙም።

የሪቨርሳይድ ክፍለ ግዛት ፖሊስ ኃላፊ ተጠርጣሪው ምን ዕቅድ እንደነበረው ማወቅ ከባድ ቢሆንም ግለሰቡ ግን ፖሊስ ፕሬዚዳንቱን ከሦስተኛ የግድያ ሙከራ እንደታደጋቸው ነው “የሚያምነው” ይላሉ። ኃላፊው አክለው የግለሰቡ ሐሳብ የግድያ ሙከራ ማድረግ ይሁን አይሁን ግን ማወቅ ከባድ መሆኑን ገልጸዋል።

ግለሰቡ በቁጥጥር ሥር የዋለው በአካባቢው ሰዓት አቆጣጠር ከሰዓት 11፡00 ሲሆን ትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ አንድ ሰዓት ቀርቷቸው ነበር። የአሜሪካ ምርጫ ድምፅ መስጫ ቀን ሦስት ሳምንታት ይቀሩታል። በየቦታው እየዞሩ የምረጡኝ ቅስቀሳ እያደረጉ የሚገኙት ዶናልድ ትራምፕ ከባድ የሚባል ጥበቃ እየተደረገላቸው ነው።

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ የግድያ ሙከራ ተደርጎባቸው እንደነበር ይታወሳል። የአካባቢው ፖሊስ ኃላፊ አክለው እንደገለፁት ተጠርጣሪው አክራሪ የቀኝ ዘመም ቡድን የሆነው ሶቨሬይን ሲቲዝንስ አባል እንደሆነ ተናግሯል። ተጠርጣሪው የያዘው መኪና የመለያ ቁጥር (ታርጋ) የሚጠቁመውም ይህን ብለዋል።

“ታጣቂ ቡድን ነው ማለት ይከብደኛል። በመንግሥት እና በመንግሥት ቁጥጥር የማያምን ቡድን ነው ማለት ይቀላል። በመንግሥት አያምኑም፤ ሕግ አይገዛንም ብለው ነው የሚያምኑት” ይላሉ ኃላፊው። ትራምፕ ከአንድም ሁለት ጊዜ የግድያ ሙከራ ስለተደረገባቸው ሲክሬት ሰርቪስን ጨምሮ ኤፍቢአይ እና ሌሎች የደኅንነት ጥበቃቸውን አጠናክረው ይጠብቋቸዋል።

ከወራት በፊት ወደ ፔንሲልቬኒያ ግዛት አቅንተው በትለር በተባለ ሥፍራ የምርጫ ቅስቀሳ እያደረጉ ሳለ የተተኮሰባቸው ጥይት ጆሯቸውን ጨርፎ ማለፉ ይታወሳል። የግድያ ሙከራ ያደረገው ግለሰብ በደኅንነት ሰዎች ሲገደል በክስተቱ አንድ የትራምፕ ደጋፊ ሕይወቱን ማጣቱ አይዘነጋም።

ባለፈው መስከረም ደግሞ ዌስት ፓልም ቢች በሚገኘው ጎልፍ ክለባቸው ሳሉ አንድ ተጠርጣሪ የጦር መሣሪያ ይዞ በመገኘቱ በቁጥጥር ሥር ውሎ ምርመራ እየተደረገበት ይገኛል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት





## የሴቶች ማራቶን ክብረወሰን ሌላ ምዕራፍ

ቦጋስ አበበ

የምሥራቅ አፍሪካ ከዋክብት አትሌቶች ለረጅም ዓመታት በተለይም በመካከለኛና ረጅም ርቀት ውድድሮች ስፖርቱን ወደፊት በማራመድ ዘመን የማይሽራቸው ታሪኮችን አኑረዋል:: ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ እያሳዩት የሚገኘው ብቃትም የሰው ልጅ የአቅም ጥግ ገደብ እንደሌለው እያስመሰከረ የማይቻል ነገር እንደሌለ አረጋግጧል::

በ19ኛው ክፍለዘመን ወንዶች ማራቶንን ለ3 ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች በሚቀሩት ሰዓት ያጠናቅቁ ነበር:: ከመቶ ዓመት በኋላ ግን ይህ ሰዓት ተሻሽሎ ከ2 ሰዓት በታች ማጠናቀቅ የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ለዚህም የምሥራቅ አፍሪካ ከዋክብት አትሌቶች የተጫወቱት ሚና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል::

የወንዶች ማራቶን ክብረወሰን ባለፉት ሃያ ዓመታት ብቻ አስር ጊዜ ተሻሽሏል:: ከነዚህ ክብረወሰኖች ውስጥ ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ የሁለቱ ባለቤት ሲሆን ሰባት ያህል ክብረወሰኖች በኬንያውያን አትሌቶች ተሻሽለዋል:: ይህም የምሥራቅ አፍሪካ የርቀቱ ኮከቦች የማያባራ ፉክክር ማራቶንን ዛሬ ለደረሰበት ታላቅነት እንዳበቁት ማሳያ ነው::

የሴቶች ማራቶንን በተመለከተ ግን ከጥቂት ዓመታት በፊት የዓለም ክብረወሰን ሌላ መልክ ነበረው:: እኤአ 2003 ላይ እንግሊዛዊቷ ታሪካዊ አትሌት ፓውላ ራትክሊፍ በለንደን ማራቶን በ2:15:25 አዲስ ዓለም ክብረወሰን ካስመዘገበች ወዲህ ለሁለት አስርተ ዓመታት ገደማ የሴቶች የማራቶን ክብረወሰን ለውጥ አልታየበትም:: 2019 ላይ ግን ኬንያዊቷ ብሪጊድ ኮስጌ በቺካጎ ማራቶን 2:14:04 በማጠናቀቅ ቆሞ የነበረውን የሴቶች ማራቶን ክብረወሰን አንድ ርምጃ ወስዳዋለች:: ይህ በሴቶች ማራቶን የማይቻል የሚመስለውን ክብረወሰን በይቻላል የለወጠ ትልቅ የታሪክ እጥፋት ነበር:: ያም ሆኖ የሴቶች ማራቶን ክብረወሰን ልክ እንደወንዶቹ በጥቂት ዓመት ልዩነት



ኢትዮጵያውያንና ኬንያውያን ከዋክብት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሴቶች ማራቶን ታሪክ መቀየር ችለዋል፣

ዳግም ሳይሰበር ለመቆየት ተገዷል::

ከአራት ዓመታት በላይ ሳይሻሻል የቆየው የሴቶች ማራቶን ክብረወሰን ዳግም እስኪሰበር ሌላ ሁለት አስርተ ዓመታት አልጠበቀም:: ከአራት ዓመት በኋላ በ2023 የበርሊን ማራቶን ብዙዎች ለማመን በተቸገሩበት አስደናቂ ብቃት ኢትዮጵያዊቷ ብርቅዬ አትሌት ትዕግስት አሰፋ ከአራት ደቂቃ በላይ በማሻሻል በ2:11:53 አዲስ ክብረወሰን ለመጨበጥ በቃች:: ይህም በሽርፍራፊ ሰከንዶች ለማሻሻል ከብዶ የነበረውን የርቀቱን ክብረወሰን በሩጫው ዓለም ሰፊ በሚባል ልዩነት ማሻሻል እንደሚቻል ከማሳየቱም በላይ የርቀቱ ኮከብ አትሌቶች የተሻለ ሰዓት እንዲያስቡ ትልቅ ተነሳሽነትን ፈጥሮባቸዋል:: ይህም ተነሳሽነት በሴቶች ማራቶን ታሪክ ከአንድ ዓመት በኋላ ሌላ አዲስ የማራቶን ክብረወሰን ለአትሌቲክሱ አበርክቷል::

ባለፈው ዓመት የወንዶች ማራቶን ክብረወሰንን ኬንያዊው ኬልቪን ኪፕተም በ2:00:35 ሰዓት ያሻሻለበት የቺካጎ ማራቶን ከትናት በስቲያ ለ46ኛ ጊዜ ሲካሄድ ኬንያዊቷ ሩት ቼፕጌቲች 2:09:56 ሰዓት በማጠናቀቅ አምና በትዕግስት የተያዘውን ክብረወሰን ከሁለት ደቂቃ ባልተናነሰ ሰዓት በማሻሻል የሴቶችን የማራቶን ክብረወሰን ወደ ሌላ ምዕራፍ አሸጋግራዋለች::

ለዚህ አዲስ ምዕራፍ መከፈት በፉክክሩ ሚና ከነበራቸው አትሌቶች አንዷ ኢትዮጵያዊቷ ሱቱሜ አሠፋ 2:17:32 በማጠናቀቅ ሁለተኛ ስትሆን ሌላኛዋ ኬንያዊት ኤሪን ቼፕታይ 2:17:52 በመግባት ሦስተኛ፣ ኢትዮጵያዊቷ ቡዜ ድሪባ 2:20:22 በሆነ ሠዓት አራተኛ ሆነው ፈጽመዋል::

50ሺ የሚጠጉ ተሳታፊዎች በተካፈሉበት የቺካጎ ማራቶን በወንዶች የዓለም ክብረወሰን አልተመዘገበም:: የ27 ዓመቱ ጆን ኮሪር 2:02:43 በመግባት አንደኛ በመሆን ሲያሸንፍ 2:04:39 በሆነ ሠዓት የገባው ኢትዮጵያዊ መሐመድ ሆሠይዲን ኢሣ ሁለተኛ፣ ኬንያዊው አሞስ ኪፕሩቶ በሦስተኛነት ማጠናቀቅ ችለዋል::

ሴቶች ማራቶንን ከ2 ሰዓት ከ20 ደቂቃ በታች ለመጀመሪያ ጊዜ ማጠናቀቅ የቻሉት እአአ 1979 ሲሆን፤ በ2ሰዓት ከ19 ደቂቃ ርቀቱን ለመሸፈን ደግሞ 22 ዓመታት ተቆጥረዋል:: እአአ ከ1970ዎቹ ወዲህ ባሉት ዓመታት አዳዲስ ክብረወሰን የተመዘገበባቸውን ጊዜያት ስንመለከትም አርባ ሁለት ኪሎ ሜትሩን የሚያጠናቅቁበት የሰዓት ልዩነት እየሰፋ መምጣቱን መገንዘብ ይቻላል::

ማራቶንን ከ2ሰዓት በታች ለማጠናቀቅ በወንዶች በኩል ከሚደረገው ጥረት እና ከፍተኛ ፉክክር አንጻር በሴቶች በኩል ከጥቂት ዓመታት በፊት ርቀቱን ከ2ሰዓት ከ10 ደቂቃ በታች ለማጠናቀቅ የሚደረገው ጥረት እምብዛም ሊባል የሚችል ነበር:: ይሁንና ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትዕግስት አሰፋ ቀድሞ ከነበረው ሰዓት ከሦስት ደቂቃ በላይ ማጠናቀቅ አሁን ላይ ሌላ የርቀቱን ፈጣን ኮከብ እንደፈጠረው ሁሉ በቅርብ ዓመታትም አዲስ ነገር ተስፋ እንዲጠበቅ አድርጋል::

የፓሪስ ኦሊምፒክ የማራቶን የብር ሜዳሊያ አሸናፊዋ አትሌት ትዕግስት አሰፋም ገና ወጣት ከመሆኗ በተጨማሪ ካላት ጽናትና ብቃት አንጻር ይህን ሰዓት አሻሽላ ክብረወሰኑን ዳግም በእጇ ለማስገባት ከወዲሁ የቤት ሥራዋን እንደምትጀምር ይጠበቃል::


## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በወላይታ ከተማ በሶዶ ከተማ አስተዳደር ወረዳ ቀበሌ ዋዱ አስተዳደር የቤት ቁጥር በ 0057467202 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለሚታወቀው የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማስገኛ ድርጅት ንግድ ድርጅት በግብር ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ከሀዋሣ ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ከምጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ -

**የተርን ኦቨር ታክስ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ (ያልተሰራበት)**

1.ከቁጥር 201 እስከ 250

2. ከቁጥር 951 እስከ 1000

3.ከቁጥር 1201 እስከ 1350

4. ከቁጥር 1501 እስከ 1600

5.ከቁጥር 1651 እስከ 1800

6.ከቁጥር 1851 እስከ 2150

7.ከቁጥር 2751 እስከ 2950

8 .ከቁጥር 4351 እስከ 4400

9 ከቁጥር 4601 እስከ 4650

**የተርን ኦቨር ታክስ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ (ያልተሰራበት)**

1. ከቁጥር 201 እስከ 250

ደረሰኝ ጥቅም ላይ ሳይውል ስለጠፋብኝ በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፉ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል:: ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸሙ በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት የ ሀዋሣ ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ እጠይቃለሁ::

**የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ገቢ ማስገኛ ድርጅት**

## የንግድ ምልክት ዕድሳት ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የባለቤቱ<br>ስምና አድራሻ | አፖሎ ታየርስ ኤ.ጂ<br>(APOLLO TYRES A.G)<br>Landis+ Gyr-Strasse 1, 6300 Zug, Switzerland |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር | FTM/4194/2010 |
| 3 | የዕድሳት ጊዜ | ከ20/04/2024 እስከ 20/04/2031 |
| 4 | የንግድ ምልክቱ | AMAZER 3G |
| 5 | ባለቤቱ ይህንን የንግድ ምልክት የሚጠቀመው በዓለም- አቀፍ ምድብ 12 በ27/08/2002 ዓ.ም. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ Vol.LXIX No.237 በወጣው ማስታወቂያ ከተዘረዘሩት ምርቶች ጋር በተያያዘ ነው:: | |
| 6 | ማንኛውም ግለሰብ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም - ከባለቤቱ ሳያስፈቅድ በዚህ የንግድ ምልክት በሚገለገል ወይም አስመስሎ በሚሠራ ላይ ይመሠረትበታል። | |

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

ADDIS ZEMEN VOI-LXXXIV No-035 - 5/2/2017 (15/10/2024)

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- ጃካራንዳ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ. 02 የቤት ቁጥር 329/702, ቦሌ, አዲስ አበባ /ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/17325/2016<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 08/12/2016 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡-  | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- የወይንጠጅ ፣አረንጓዴ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡ .(Tour and Travel PLC ) |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 39 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | አስጎብኚ እና የጉዞ ወኪል(ምድብ 39) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

ADDIS ZEMEN VOI-LXXXIV No-035 5/2/2017 (15/10/2024)